# ሮቢንሰን ክሩሶና ሕወሓት-ጦርጦስ

## ወቅታዊ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት ትንተና
## ልማት ወይስ ፅዳት?

አየለ ታደሰ*

Aug 2014

አጭር መግለጫ
ይህ ጦማር አሁን ባለው የኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት ዙሪያ መጠነኛ ትንተና ለማቅረብ ያዘጋጀሁት ሲሆን በተለይም የ"አንድ ሰው ምጣኔ ሃብት" ከሚለው ፅንሰ ሃሳብ ጋር በማዛመድ ለየት ያለ የአቀራረብ ዘዴ በመጠቀም የ"ዘመናችንን" የሕወሓት-ጦርጦስ ምጣኔ ሃብትን ለመቃኘት ሞክሬያለሁ። ይህ ጦማር ከሚዳስሳቸው ነገሮች ውስጥ ሮቢንሰን ክሩሶና ሕወሓት የሚመሳሰሉትና የሚለያዩበት ፀባያት ምንድናቸው? በሚል አስተሳሰብ ዙሪያና ምጣኔ ሃብታዊ የሂሳብ ስሌቶችን በመዳሰስ የተለያዩ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ያነሳል። ከነዚህም አንገብጋቢ የወቅቱ ሁኔታዎች ውስጥ፤ ለምሳሌ ያህል "ምግብ ወደውጭ ዓለም በመላክ (By Exporting food items) ምን ጥቅም ተገኝቶበታል?" "በአገራችን እየተካሄደ ያለው የቤቶችና የመንገድ ግንባታ ወጪው በሌላ መንገድ ቢሰላ ምን ያህል ይሆናል?" "ቴሌ በተንቀሳቃሽ ቴሌፎን ብቻ ምን ያህል ገቢ ያገኛል?" "ወደ ዓረብ አገር የሚጋዙት ወጣቶች ምን ያህል የገንዘብ ትርፍ ተገኝቶባቸዋል?" "ከህፃናት ሽያጭስ?" "ሕወሓት ከቀረጥስ ምን ያህል ገቢ ያገኛል?" "የሕወሓት የገንዘብ ምንጮቹ ምንድናቸው?" የሚሉትን ሃሳቦች ተራ በተራ ይዳስሳል።
ለመሆኑ ሕወሓት ይህንን ሁሉ ንብረት የሚሰበስበው ወይም የሚመዘብረው ምን ሊያደርግ አስቦ ነው? ይህንን በተመለከተ በዚህች ፅሁፍ በተግባር ዓይናችን ስር እያየነው ያለውን በተለይም ልዩ "የአገር ንብረት ውድመትና የምዝበራ ታሪክ አጋጣሚ" ነውና የምጣኔ ሃብት ምሁራን ትንተናቸውን ወደፊት በኢትዮጵያ የምጣኔ ሃብት ታሪክ ዙሪያ እንደሚስኮመኩሙንና ለመጪው ትውልድም የታሪክ አሻራ ትቶ ማለፍ አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑበት እርግጠኛ ነኝ።
ዛሬ ላይ ሆኜ ስመለከተው ግን ሕወሓት-ጦርጦስ በምጣኔ ሃብት በኩል እያካሄደ ያለው ምንድነው? ልማት ወይስ ፅዳት?

ክፍል አንድ

# 1. መግቢያ

ከአርዕስቱ ሃሳብ ልነሳ - ሮቢንሰን ክሩሶ ማነው? ሕወሓት-ጦርጦስ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የተጠቀምኩት ምንን ለማሳየት ነው?

በመጀመሪያ ሕወሓት-ጦርጦስን ምን ማለት እንደሆነ በሁለት መንገድ ለማሳየት ወደድሁ።

፩) "ሕወሓት" — "ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ" ወይም የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር - በ1991 ዓ/ም ከጫካ ወጥቶ ወደስልጣን የወጣ የባንዳ ርዝራዦች ጥርቅም ቡድን የሚለውን ያመላክታል። ባንዳ ማለት ደግሞ የአገሩን ጥቅም አሳልፎ ለውጭ ጠላት መስጠት ወይም ከጠላት ጋር አብሮ መስራት ማለት ነው።

እንጦርጦስ ማለት ደግሞ መቀመቅ፤ ጥልቀቱ የማይታወቅ የጭለማ ጉድጓድ ማለት ነው[1]።

ሁለቱን አሳቦች በማዋሃድ ሕወሓት-ጦርጦስ ማለት የሕወሓት ቡድን በሚተገብረው ሁሉን አቀፍ ዘመቻ አገሪቱን ወደ ማይታወቅበት ቦታ እየመራት መሆኑን ለማሳየት የተፈጠረ ፅንሰ ሃሳብ ነው።

፪) በሌላኛው ትርጉሙ ደግሞ ጦርጦስ የሚለው ሲተነተን "ጦር" ማለት ለውጊያ የሚያገለግል መሳሪያ ነው። "ጦስ" የሚለው ደግሞ መዘዝ የሚለውን ያመላክታል።

ሕወሓት-ጦርጦስ የሚለው የአገሪቱን ነዋሪ በጦር መሳሪያ በማስፈራራት "በመሳሪያ ስለወጣሁ … የፈለግሁትን አደርጋለሁ… ምንም አታመጡም … በመሳሪያ አውርዱኝ" የሚለው የዕለት ተዕለታዊ ዘመቻውን ለማመላከት ነው።

በሁለቱም ትርጉም ውስጥ የምናየው የሕወሓት-ጦርጦስ ዘመቻው ከተራ ወሮበልነት እስከ አስተዳደራዊ ሙሰኝነት ብሎም እስከ ዓለምአቀፋዊ እኩይ ተግባራቱን የሚጠቀልል ፅንሰ ሃሳብ ነው። እውነቱን ለመናገር ይህ የሕወሓት-ጦርጦስ ዓይነት አስተዳደር ከዚህ በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥም እንኳን ተሰምቶም ሆነ ተደርጎም አይታወቅም።

ለመሆኑ ሮቢንሰን ክሩሶ[2] ማነው?

የሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክ እንደዚህ ነው። ዘመኑ የ18ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አስር ዓመታት ውስጥ ማለትም ከ1704 እስከ 1709 ላይ የሚያተኩር የታሪክ ወቅት ነው። የእስፔይን የባህር ላይ የንግድ መርከቦች ወርቅና ብር ተሸክመው ከእስፔይን የቅኝ ግዛቶች ወደ እስፔይን ያግዙ ነበር። የእንግሊዝ የባህር ላይ የንግድ መርከብ ዘራፊዎችም በአውሮፓ ውስጥ በተከሰተው የጦርነት ሁኔታ በመጠቀም ዘረፋውን አጧጡፈውት ነበር።

አሌክሳንደር ስልከርክ የተባለ የስኮትላንድ ተወላጅ የሆነ ግለሰብ ከነዚህ መርከቦች ውስጥ በአንዱ መርከብ ላይ ተሳፍሮ ነበር። ታዲያ አሌክሳንደር ስልከርክን የያዘችው ወይም እሱን የጫነችው መርከብ በፓስፊክ ባህር ዳርቻ በምትገኘው የቺሊ ደሴት ላይ ትደርስና አንድ እክል ይገጥማታል። ታዲያ አሌክሳንደር ስልከርክ መርከቧ ስትቆም ለእድሳት መሆኑን ይገምትና ከመርከቧ ይወርዳል። በዚህ አጋጣሚ ሌሎች ተሳፋሪዎች የመርከቡን አዛዥ እንዲሄድ ስላስገደዱት መርከቧ ጉዞዋን ትቀጥላለች። አሌክሳንደር ስልከርክ በመርከቧ ላይ ሳይሳፈር ይቀራል። አሌክሳንደር ስልከርክ ለብቻው በዚህች ደሴት ላይ መኖር ጀመረ። በዚህች የቺሊ ደሴት ላይም ለአራት ዓመታት ከአራት ወራት ለብቻው ኖሯል።

ታዲያ "ሮቢንሰን ክሩሶ" በአንድ ብቻውን ደሴት ላይ በኖረ ግለሰብ ህይወት ዙሪያ የሚያውጠነጥን ታሪክ ሲሆን በ1719 የተፃፈ መፅሐፍ ስም ነው። ሮቢንሰን ክሩሶ በመጠኑም ቢሆን የሚተርከው የአሌክሳንደር ስልከርክ የህይወት ታሪክ ነው ይባላል። ታሪኩ ለየት የሚያደርገው ሮቢንሰን ክሩሶን ይዞት የመጣው መርከብ ምናልባትም በአውሎ ነፋስ ምክንያት ወደ ደሴት ዳርቻ እንደተወሰደና ደሴቷ ላይ የኖረ የግለሰብ ስም እንደነበር ይተርካል። በነገራችን ላይ ከእ.አ.አ. 1966 ጀምሮ የዚህች የቺሊ ደሴት ስም ሮቢንሰን ክሩሶ ተብላ መጠራት ጀመረች።

ታዋቂው እንግሊዛዊ ገጣሚ ዊሊያም ኮውፐር "ንጉስ ነኝ..." በሚለው ግጥሙ አሌክሳንደር ስልከርክን እንደዚህ ተቀኝቶለታል። በጥሬ ትርጉሙ

ንጉስ ነኝ፡ አዛዥ ነኝ፤
እኔ ነፃ ነኝ እኔ ጌታ ነኝ፡
ለምቃኘው ሁሉ በዙሪያዬ
ያሻኝን የማደርግ በቀዬ
ከየብስ መሃል እስከ ሰማይ ዳርቻ
ከምድር መሃል እስከ ባህር መባቻ
ለአዕዋፍና ለእንስሳት እኔ ጌታ ነኝ
ማንንም የምገዛ እኔ ንጉስ ነኝ።

የሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክ - በምጣኔ ሃብት ጠበብቶች ዘንድ "የአንድ ሰው ምጣኔ ሃብት[3]" (One man Economy) ምሳሌ ነው ይባላል።

ታዲያ ስለሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክ ይህን ያህል ለመግቢያ ያህል ከሰነዘርኩ፤ ለመሆኑ የሮቢንሰን ክሩሶና የሕወሓት ታሪክ ምን ያገናኛቸዋል? የሚል ጥያቄ ሊያጭር ይችላል። ተገቢ ጥያቄ ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ታሪኩን በየተራ ማለትም የሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክና የሕወሓት ታሪክ እየነጣጠልኩና እያነፃፀርኩ ማሳየት ሊኖርብኝ ነው ማለት ነው።

## 2. ልዩነት

የሁለቱን ባለታሪኮች ልዩነቶቻቸው በአጭሩ ላስቀምጥ።

**ሮቢንሰን ክሩሶ**
ሮቢንሰን ክሩሶ አንድ ግለሰብ ነው።

**ሕወሓት**
ሕወሓት ደግሞ በተወሰኑ ግለሰቦች የታጀበ ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን የጨበጠ አንድ የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ነው።

**ሮቢንሰን ክሩሶ**
ሮቢንሰን ክሩሶ በህይወት የሚንቀሳቀስ፤ ከስጋና ከደም የተፈጠረ የስው ፍጡር ነው።

**ሕወሓት**
በአንፃሩ ደግሞ ሕወሓት ህይወት አላቸው ተብለው በሚገመቱ ነገር ግን ከስጋና ከደም ባልተፈጠሩ፤ “የሰው ፍጥረት” የሚባል ባልነካካቸው፤ የሚመራ ግዑዝ ድርጅት ነው። ነገር ግን በአስተሳሰብና በድርጊት እንደ አንድ ግለሰብ ሲናበቡ እናያቸዋለን - በወል ስማቸው ግን ሕወሓት ነው።

## 3. አንድነት

ሮቢንሰን ክሩሶና ሕወሓት በምጣኔ ሃብት፤ በአስተዳደርና፤ በስነ ልቡና ዙሪያ እጅግ ተመሳሳይነት አላቸው። ተመሳሳይነታቸው እንዴት ሊገለፅ ይችላል? የሮቢንሰን ክሩሶና የሕወሓት ታሪክ በምጣኔ ሃብት በኩል ሲተነተን እንደዚህ ነው።

### 3.1 ባለቤትነት

፩) ***ሮቢንሰን ክሩሶ***

ሮቢንሰን ክሩሶ ያረፈባት ደሴት ብዙ ሃብት የነበራት በመሆኗ በጎችንና ፍየሎችን እያደነ አርዶ ይበላ ነበር። ደሴቷ ለም መሬት ስላላት አትክልት ሲያስፈልገውም እየተከለ፤ እያረሰ ምግብ ያመርትባታል። ለመኖሪያ ቤት የሚያስፈልገውንም እንጨት በነፃ እየቆረጠ ደስ ባሰኘው ቦታ ላይ መርጦ ቤት ይቀልሳል። ሮቢንሰን ክሩሶ ከሚመጡበት አደገኛ አውሬዎች ለመታደግ የራሱ የሆነ መሳሪያም ይሰራ ነበር።

ሮቢንሰን ክሩሶ ብቻውን በደሴት ላይ ሲኖር “ህይወቱን ለማቆየት ወይም ለመኖር ሲል” ለመመገብ እንሰሳት ማደንና እርሻ ማረስ፤ ለመኖሪያነት የሚጠቅመው - የሚኖርበትን ቤት መስራት፤ ከቁርና ከብርድ ለመከላከል - የሚለብሰውን ልብስ ማዘጋጀት ይኖርበታል። ለብቻው ያመርታል፤ የሚያመርተውን ምርት ተጠቃሚ እሱ ብቻ ነው። በሌላ አባባል ሲገለፅ - ሮቢንሰን ክሩሶ አራሽም፤ አምራችም፤ አዳኝም፤ ሸማችም፤ ለባሽም፤ ተጠቃሚም፤ ተመጋቢም፤ ጦረኛም፤ ተዋጊም ነው። በአጭሩ ሮቢንሰን ክሩሶ ሁሉንም ነው።

***ሕወሓት***

ሕወሓት ደግሞ ልክ ሮቢንሰን ክሩሶ በኢትዮጵያ የሚገኙትን ማንኛቸውም ድርጅቶች በሞኖፖል የያዘ “ባለቤት” ነው። ሮቢንሰን ክሩሶ በጎቹ ለሚበሉት ሳር አዛዥ / ባለቤት እንደሆነ ሁሉ ማለት ነው። በቅርቡ ይፋ በሆነው መረጃ መሰረት በአገሪቱ ውስጥ ካሉት አነስተኛ ድርጅቶች ውስጥ 4% ወይም 5% የሚሆነው የተያዘው በኢትዮጵያውያን ነው። በአገሪቱ ውስጥ ካሉት ትላልቅ፤ መለስተኛና አነስተኛ ድርጅቶች ውስጥ 95% ወይም 96% የተያዙት በሕወሓትና በጥቂት ተለጣፊ ግለሰቦች ነው። ስለሆነም

አብዛኛው በኢትዮጵያ የሚገኙት ድርጅቶች የሕወሓት ናቸው። ትላልቅ ድርጅቶችና ፋብሪካዎች የኤፈርት ናቸው። ኤፈርት ደግሞ የሕወሓት ነው። ኢትዮጵያውያን የሚመኩበት "የኢትዮጵያ አየር መንገድ" የሕወሓት ነው። ባንኮችና የመድን ድርጅቶች የሕወሓት ናቸው። እቃ አስመጭዎች/አከፋፋይ ድርጅቶች የሕወሓት ናቸው። ሲሚንቶ አምራች ድርጅቶች የሕወሓት ናቸው። የምግብ አምራች ድርጅቶች የሕወሓት ናቸው። የኢትዮጵያ የገጠርና የከተማ መሬቶች የሕወሓት ናቸው። የኢትዮጵያ ወንዞችና ደኖች የሕወሓት ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገነቡት ፎቆች የሕወሓት ናቸው። ሌላው ቢቀር በመሬቷ ላይ የሚገኙት የሰው ልጆች (ገበሬዎች፤ ሰራተኞች፤ ህፃናቶች፤ ወጣቶች፤ አባቶች፤ እናቶች፤ ወታደሮች፤ አእዋፍት፤ የዱርና የቤት እንሰሳት ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ነዋሪዎች ሁሉ) የሕወሓት ንብረት ናቸው። ሌላው ቢቀር ሕወሓት እጁን በማስረዘም በውጪ የሚገኙት ኢትዮጵያውንና ንብረታቸውንም ጭምር የራሱ ለማድረግም እየጣረ ይገኛል። ሕወሓት ልክ ለሮቢንሰን ክሩሶ ታዋቂው እንግሊዛዊ ገጣሚ ዊሊያም ኮውፐር "ንጉስ ነኝ…" ተብሎ እንደተቃኘለት ሁሉ ሕወሓትም በዓይኑ ለሚቃኘው ሁሉ ነገር ንጉሥም፤ ገዢም ነው።

…
ንግድና … የምጣኔ ሃብት፥
ዳኝነት ትምህርትና … ንብረት፤
የትግራይ "ወዳጆቼ" … እንዲንበሸበሹበት፥
የስልጣን እርከን … እንዲይዙበት፥
ዘጠና ዘጠኙ ግን… እንዲያጠፉበት፤
የስለላው አውታር … ዘርግቻለሁ፥
የሩቅ ትልሜን …. ነድፌያለሁ፤
… *"የዘርማንዘሬን ብለቅ …." አሉ አቶ መለሰ - ከሚለው ግጥም የተወሰደ*[4]

ሕወሓት እንደ ግዑዝ ግን ልክ እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ በአንድ ጭንቅላትና አቅጣጫ ብቻ የሚያስብ ነው። ሕወሓት በ"መለሰ" ጭንቅላት የሚሽከረከር ግን እንደ መለሰ ግዑዝ በድን ነው። ሕወሓት እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ በጎችን፤ ፍየሎችንና ከብቶችን ያሉበትን ቦታዎች እያደነና እየዘረፈ፤ እንዲሁም የአገሪቱን የምጣኔ ሃብት በጉልበት እየዘረፈ ለራሱ ፍላጎትና እርካታ የሚያውል፤ ለመኖሪያ ቤቶችም ሆነ የገጠር መሬቶችን የሚያስፈልገውን መሬት መርጦ ነዋሪዎችን በማፈናቀል ለራሱ የሚጠቀም ይወስዳል ሲያሰኘው ደግሞ በርካሽ ዋጋ እየቸበቸበ ወይም እንዳሻው በነፃ ለውጪ ዜጋ ይሰጣል።

የሕወሓት የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ዋናው ዓላማ የዓላማው አስፈፃሚዎችና ተከታዮች የሆኑት እጅግ በጣም ጥቂቶቹ የትግራይ ተወላጆች ሃብታም እንዲሆኑ ሁሉንም መንገድ (ማለትም የምጣኔ ሃብት ፖሊሲውንም ጨምሮ ማለት ነው) ያመቻቻል። በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በድህነት አለንጋ እየተገረፈ በቁሙ እንዲሞት (በምጣኔ ሃብት ፖሊሲም ጭምር) ተፈርዶበታል። አንድ የተወሰነ የኅብረተሰብ ጥቂት ክፍል ያለመጠን ሃብታም ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል በድህነት ማጥ ውስጥ ይዳክራል። በምጣኔ ሃብት እድገት ህግ መሰረት አገራችን ካለችበት ችግር ልታንሰራራ የምትችለው በመካከለኛው የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲበረክቱ ነው። ስለዚህ የሕወሓት የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ስለ ሕወሓትና ሕወሓት ብቻ የሚያማክል ስለሆነ እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ የ"አንድ ሰው የምጣኔ ሃብት"ን ይመሳሰላል።

**ክፍል ሁለት**

## 3.2 ብቸኝነት

፩) **ሮቢንሰን ክሩሶ**

ሮቢንሰን ክሩሶ ሌላ ሰው በማይኖርበት ቦታ ላይ የሚኖር በመሆኑ የሚፈልገውንም የሚያደርገው ብቻውን ነበር። ሮቢንሰን ክሩሶ ትልቁ ችግሩ ብቸኝነት ያጠቃዋል። እየሰመጠችው ከነበረችው መርከብ ውስጥ ካገኛቸው ነገሮች መካከል መፅሐፍ ቅዱስና የመርከብ መንገድ ማሳያ ጠቋሚ ካርታዎች እንዲሁም ለአውሬ መከላከያ የጦር መሳሪያዎች ነበሩበት። ታዲያ ብቸኝነትን ማባረር ሲፈልግ የሚያነባቸው መፅሐፍ ቅዱስና ካርታዎቹን ነበር። ሮቢንሰን ክሩሶ ለብቻው ብዙ ሰው እንዳለ አድርጎ በማሰብ የሚያነባቸውን ታሪኮችን መልሶ መላልሶ ይተርክ ነበር። በሌላ አባባል ሮቢንሰን ክሩሶ ብዙ ሰው መስክ ላይ አድርጎ በማሰብ ወደ መስክ ወጥቶ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይተርክ ነበር። አንዲት በቀቀን ወፍንም አንዳንድ ቃላቶችን ማስተማርም ችሎ ነበርና አንድ ጊዜ ከእንቅልፉ እንዳባነነችው በታሪኩ ላይ ተወስቷል። ወይጉድ ብቸኝነትም እኮ የራሱ የሆነ የስነ-ልቡና ችግር አለው።

**ሕወሓት**

ሕወሓት ጫካ እንደነበረ የፃፈው *መመሪያ*፤ የነደፈው የራሱ ካርታ አለው። ወደ ስልጣን ሲወጣም የሚያነበው ያንኑ "*መመሪያ*"ና ካርታ ነው። አቦይ ስብሃት እንደመሰከረው ይህ ጫካ ውስጥ የተፃፈው *መመሪያና* የተነደፈው የትግራይ ካርታ ሕወሓት "እንደ *መፅሐፍ* ቅዱሳችንና ካርታችን የችግራችን ብቸኛ ቁልፍ መፍቻ" ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም ያንኑ ያጠናውን "*መመሪያና* ካርታ" ባለው ሰፊ የዜና ማሰራጫ መድረኮቹ በመጠቀም ብዙ ሰው እንደሚያዳምጠውም አድርጎም በማሰብ ከድሮ ጀምሮ ያጠናውን መልሶ ይተርካል ወይም ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነባል። ሕወሓት የራሱን "በቀቀን ወፎችንም" አሰልጥኗል። ሕወሓት "ልማት" ወይም "አሸባሪ" ሲል ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "ልማት" ወይም "አሸባሪ" ብለው የሚደግሙለት በቀቀኖችን አስተምሮ በህዝቡ መሃል አዝምቷል። ትልቁ የሕወሓት ችግሩ ብቸኝነቱ ነው። ማንኛውንም ነገር የሚያደርገውም ለብቻው ነው። ገንዘብ ሲዘርፍ ለብቻው። በንግድ ዓለም ሲሰማራ ለብቻው። ሲያጠምድ ለብቻው። ሲበላ ለብቻው። የአገሪቱን ሃብት ሲያጋብስ ለብቻው። ሌሎቹን የአገሪቱ ነዋሪዎችን አያማክርም። ታዲያ እዚህ ላይ ልብ ያለው ልብ ይበል - ሕወሓት የአገሪቱን ንብረት ሁሉ ዘርፎ ሲወድቅ ግን ለብቻው አይወድቅም። አገሪቷም አብራ ትወድቃለች። ይህ ማለት ደግሞ ሕወሓት መንበረ-ስልጣኑን እንደጨበጠ ይቀመጥ ማለት ሳይሆን እንዲያውም መንበረ-ስልጣን ላይ በቆየ ቁጥር ከዚህ የበለጠ ለአገር የሚያመጣው ጦስ አለውና…። የሕወሓት ዓይነት ብቸኝነት ደግሞ በዘመናዊው ዓለማችን ከሮቢንሰን ክሩሶ ወቅትና ጊዜ የበለጠ የራሱ ልዩ የሆነ የስነ-ልቡና ችግር አለው።

## 3.3 የህዳጉ ዋጋ ለውጥ

፫) **ሮቢንሰን ክሩሶ**

ሮቢንሰን ክሩሶ ፍየሎችንና በጎችን ለማደንና ለማዘጋጀት የሚያጠፋው ጊዜ፤ ወይም ደግሞ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለመዝራትና ለመሰብሰብ ከሚያጠፋው ጊዜ ጋር ሲወዳደር ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል። ብዙ ጊዜውን በማደን ላይ ካጠፋ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለመልቀም የሚኖረው ጊዜ አነስተኛ ይሆናል። ሮቢንሰን ክሩሶ የአትክልትና ፍራፍሬዎች ብዛትና መጠን መቀነስ ብዙ ሥጋ ለማግኘት ስለሆነ፤ አትክልትን ለማምረት ያሚያጠፋው ጊዜ በመቀነሱ (የስጋ ብዛትና መጠን ለመጨመር ማለት ነው።) ይህ የሚያካክሰው ጊዜ የህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) ተብሎ ይጠራል።

**ሕወሓት**

ሕወሓት ደግሞ የህይወት እስትንፋሱን ለማራዘም በሁለት ነገሮች ዙሪያ የሚያጠፋውን ጊዜ ለማጣጣም ሲታገል እናያለን። <u>ገንዘብ ማሰብሰብ</u> እና <u>ካድሬዎችን ማበራከት</u>።

ሕወሓት <u>ገንዘብ ለመሰብሰብ</u>ና አቅጣጫ ማስቀየስ ሲፈልግ አገራዊና ስሜትን የሚነኩ እቅዶችን ያቀርባል። እቅዱን ለማጥናትና ለመንደፍ የሚያጠፋው ጊዜ ግን አጭር ነው። ሌላው ቢቀር ለምሳሌ አንድ መኖሪያ ቤት ከመገንባቱ በፊት ስለቤቱ አሰራር ጥናት መደረግ ይኖርበታል። ቤቱ የሚሰራበት ቦታ፤ የግቢው ስፋት፤ ቤቱ የሚቆምበት መሬት ስፋት፤ ቤቱ ስንት ክፍሎች እንደሚኖሩት፤ መፀዳጃና የምግብ ማብሰያ ክፍሎች፡ የመብራትና የውሃ አቅርቦት ... ወዘተ። ጥናት ለማጥናትና ንድፍ ለማዘጋጀት ሰፋ ያለ ጊዜ ይፈልጋል። በተለይም አገራዊ ይዘት ያላቸው እቅዶች ሰፊ ጥናትና ጊዜ፤ ብዙ ውይይት ይፈልጋሉ። በስሜት የተካኑ ግን ጥናት ያልተደረገባቸው የሕወሓት እቅዶች አገር "አጥፊ" ናቸው። ስለሆነም አገራዊና ስሜት የሚነኩ የሕወሓት እቅዶች የሚጠብቀውን ያህል ውጤት አያመጣለትም። ከነዚህ አገራዊ ስሜት የሚነኩ እቅዶቹ ወይም ንድፎቹ ውስጥ ለምሳሌ ሴቶች እህቶቻችንን "በሥራ ስም" ወደ አረብ አገር ማጋዝ፤ መሬትን "በልማት ስም" ለውጭ ባለ ሃብቶች መቸብቸብና፤ የቤቶች ግንባታ፤ የ"አባይ ግድብ ግንባታ"፤ እና የመሳሰሉትን ማየት እንችላለን። አቅዶቹን ለማጥናት የሚያጠፋው ጊዜ እጅግ በጣም አጭር ነው። ቅፅበታዊ ነው። እነዚህን ሃሳቦችን ከመንደፉ በፊት ሰፊ ጥናት አያደርግባቸውም። ገንዘብና የራሱን የስልጣን እርካታ እስካስጠበቀለት ድረስ በአንድ ሌሊት ድንገት እንደባነነ ሰው ብድግ ብሎ ባልታሰበ መንገድ ተፈፃሚ ለማድረግ ይነሳል። እነዚህና የመሳሰሉት እቅዶች ጥናት የተደረገበት በማስመሰል ካድሬዎቻቸው የውጭ አገራትን ምሳሌ በመስጠት ሲያጣቅሱ ስንሰማ አበው እንደሚሉት "የሌባ አይነደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ" ዓይነት ጥናትና መረጃዎችን ያላማከለ "አገር አጥፊ ንድፎች" ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ <u>ካድሬዎቹን ለማበራከት</u> የሚፈጅበት ጊዜ ረዘም ያለ ነው። በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሰፋፊ የማጥመጃ መረብ እጁን በመዘርጋት፤ የምጣኔ ሃብት አጋብሶ (በፊት ሁሉም ነገር ወደ ትግራይ ነበር አሁን ደግሞ ወደተለያየው የዓለም ክፍል ሆኗል - የተሻሻለ ዘመናዊ ዓላማው)፤ ሙስናን በአገሪቱ ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅና እግሩን እንዲሰድ፤ ትውልዱን እንዲኮላሽ ለማድረግ የአልኮልና የአሽሽ ልማድ ሱስ ተገዢ እንዲሆን አድርጎታል። ታዲያ ሕወሓትም እንደሮቢንሰን ክሩሶ የህይወት እስትንፋሱን ለማቆየት ሲል ሁለቱን ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚፈጅበትን ጊዜ ተመጣጣኝ የማድረግ "ችሎታ" ይጠበቅበታል። <u>ገንዘብ ለመሰብሰብና ካድሬዎችን ለማበራከት</u> የሚያጠፋው ጊዜ የህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) ተመጣጣኝ መሆን ይጠበቅበታል።

ሮቢንሰን ክሩሶ የስጋውን መጠን ለመጨመር ጊዜውን አትክልት ለመሰብሰብ ከሚያጠፋው ጊዜ ላይ እንደጨመረ ሁሉ ሕወሓት ደግሞ "<u>ካድሬዎቹን ለማበራከት</u>" የሚያጠፋውን ጊዜ የሚወስደው ከ<u>ገንዘብ ለማሰባሰቢያ የሚበጀው እቅድ ወይም ንድፍ ጊዜ</u> ላይ በመሆኑ በህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) ሳቢያ ወደ ከፍተኛ ኪሳራ እንደሚያመጣው ከቶውንም ሊከሰትለት አልቻለም። እንዴት ሊያከስረው ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊያጭር ይችል ይሆናል።
ካድሬዎችን ለማብዛት የሚደረገው ግፊት በራሱ ወጪው እጅግ ከፍተኛ ነው። ገንዘብ የማሰባሰብ ኃይሉ እየተዳከመ ከሄደ ለካድሬዎቹ የሚከፍለው ገንዘብ ስለማይኖርው ካድሬዎቹ የሕወሓትን ሥር ሊያቀጭጩት ይችላሉ። ለ"ደህንነቱም" ቢሆን ገንዘብ ያስፈልገዋል። አሊያ ግን ወታደራዊው ክፍል ፊቱን ሊያዞርባቸው ይችላል። የወታደራዊው ክፍል አዛዦችም ቢሆኑ በሙስና የተጨማለቁ ናቸው። ለዚህ ምስክር የሚሆነው 1) የቀድሞ የሕወሓት ውስጥ አዋቂ ግለሰቦች በኢሳት የዜና ማሰራጫ ላይ እየቀርቡ የሚሰጡት መረጃዎች 2) ሕወሓት በወታደሩ ገንዘብ አወጣጥ በኩል ማንኛውም ዓይነት የገንዘብ ቁጥጥር (Audit) እንዳይደረግ በህግ ማፅደቁ 3) የሕወሓት አምላኪ ትግራይ ተወላጆች በዙሪያው ማሰባሰቡ ነው። ይህ ሁሉ ዘዴዎችን መፈየዱ ሚስጥር እንዳይወጣ ለማድረግ ነው። በዚህ ዘመን አንድ ድርጅት ወይም አካል በገንዘብ ኃይል የሚንቀሳቀስ ከሆነና የገንዘብ ቁጥጥር (Audit) የማይፈልግ ከሆነ ትልቅ በሽታ አለበት ማለት ነው። ልማትና ብልፅግናን ለማምጣት የገንዘብ ቁጥጥርን ማሳደግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነውና።

እዚህ ላይ ልብ በሉልኝ በሮቢንሰን ክሩሶና በሕወሓት መካከል ካሉት ልዩነቶች መካከል አንዱ በገንዘብ ላይ ያላቸው ልዩነት ነው። ከሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክ ላይ እንደምንረዳው ሮቢንሰን ክሩሶ ሌባ አይደለም። አልሰረቀም። አልዘረፈም። የሰው ህይወትም አላጠፋም። ነገር ግን ጀብደኛ ነው።

ወደ ባህር እየሰመጠች ካለችው መርከብ ላይ ብዙ የሚያስፈልጉትን ነገሮችን በማትረፍ አሸሿል። እንዲያውም ከነዚህም ነገሮች ውስጥ አንዱ 18 ኪሎ የሚመዝን የአውሮፓና የብራዚል የገንዘብ ክምችት (ወርቅና ብርን ሳይጨምር) ነበር። እነዚህ ገንዘቦች በወቅቱ የመገበያያ ዋጋ ነበሩ። ታዲያ ሮቢንሰን ክሩሶ የገንዘብ ክምችቱን ሲያገኝ በትዝብት አንስቶ እያየ "አንተ ገንዘብ ሆይ! እዚያ አገሬ እያለሁ ባገኝህ ኖሮ ብዙ ነገር ልሸምትና ልጠቀምብህ በቻልኩ ነበር። ሃብታም ሆኜ ከአገሬም ለቅቄ ባልወጣሁ ነበር። አሁን ግን ጠልቄ ካለሁበት የብቸኝነት ኑሮ ልታወጣኝ አትችልም።" አለው። በተቃራኒው ደግሞ የሕወሓት እስትንፋስ የተመሰረተው በገንዘብ ላይ ነው። ገንዘብ የሚያወጣና የሚያስገኝለት ከሆነ እንኳን ኢትዮጵያንና ልጆቿን አይደለም - "በልማት ስም" በአምላክ መልክ ራሱን ተክቶ ተፈጥሮን በመገደብ "ፀሐይ" እና "አየር" ለኢትዮጵያውያን ከመቸርቸር እንደማይመለስ እርግጠኛ ነኝ። ሁኔታውን ለማሳየት አንድ አናሳ ምሳሌ ላንሳ።

> *ሕወሓት ወደ ውጪ አገር ለ"ቤት ውስጥ ስራ" በመላክ ያገኘው የምጣኔ ሃብት ትርፍ ሂሳቡን በማስላት በቁጥር ላሳይ። ይህ የእኔ ስሌት በቀጣሪና አስቀጣሪ መካከል የሚከፈል ክፍያ ወይም ሕወሓት ከቀጣሪ አገራት የሚያገኘውን ጥቅማ ጥቅም እዚህ የሒሳብ ግምት ውስጥ አልተካተተም።*
>
> 400 ሺ ወጣቶች ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ፤ ለዚያውም ገና በለጋ እድሜያቸው፤ ወደ አረብ አገራት በ"ሕወሓት የልማት እቅድ" መሰረት ወጥተዋል ተብሎ በዜና ማሰራጫዎች አድምጠናል። አንብበናልም። ወደ አዲስ አበባ በሄድኩበትም ጊዜ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ወደ አረብ አገር ተጓዥ ከነበሩት ወጣት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዲቷ ኢትዮጵያዊ እህቴ እንደነገረችኝም ከሆነ ይህንን ጉዞዋን ለማስፈፀም ብቻ ከ7,000 - 10,000 ሺህ የኢትዮ ብር ወጪ አድርጋለች። ለዚያውም የአውሮፕላኑን የጉዞ ወጪ ሳይጨምር ማለት ነው። አብረዋት የነበሩትም ወጣቶች ነገር ግን ከሌላ ቀዬ የመጡትም ይህንኑ አረጋግጠውልኛል። ከየት አካባቢ ነው የመጣችሁት ብዬ ስጠይቃቸው ከኖሩበት ቀዬ ውጪ ሌሎችን አካባቢዎች (ወረዳና አውራጃ) እንኳን የማያውቁ ለግላጋ ወጣቶች ነበሩ። ታዲያ የአገራችን ገበሬዎች ይህን ያህል ገንዘብ ከየት አምጥተው ነው የከፈሉላችሁ ብዬ ስጠይቃቸው ሁሉም የሰጡኝ መልስ ወላጆቻቸው በብድር እንዳገኙና እነሱ ማለትም ተጓዦቹ ልጆች አረብ አገር ደርሰው ስራ ሰርተው ከሚያገኙት ገንዘብ እንደሚከፍሉ ነበር ያዋዩኝ። የሕወሓትን ደባ ሳይረዱ፤ ተስፋ ሰንቀው፤ ትልቅ የአደራ ሸክም ተሸክመው፤ ወደ አረብ አገራት አቀኑ። አደራውም ወላጆቻቸው የተበደሩትን ገንዘብ ሰርተው ለመክፈል ነበር።
>
> እንግዲህ ከላይ በቀረቡት መረጃዎች መሰረት
>
> 1) ወደ አረብ አገራት የሄዱት 400,000 አራት መቶ ሺህ ወጣቶች ናቸው።
> 2) እያንዳንዳቸው እስከ 10,000 ሺህ የኢትዮ ብር ወጪ አድርገዋል።
> 3) በዚህ የስራ መስክ የተሰማሩት የሕወሓት ድርጅቶች ባጠቃላይ 400 ድርጅቶች ሲሆኑ ፈቃድ ያላቸው 20 ድርጅቶች ናቸው ተብሏል።
>
> በዚህ ስሌት የሕወሓት ድርጅቶች በትንሹ ከነዚህ ወጣቶች በትንሹ (4,000,000,000 የኢትዮ ብር) <u>አራት ቢሊዮን የኢትዮ ብር</u> ሰብስበዋል ማለት ነው። ይህ እንግዲህ በኔ አናሳ የሂሳብ ስሌት ነው። አቦይ ስብዓት ቪ.ኦ.ኤ ላይ ከአዲሱ ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ የኤፈርትን ግዙፍነት እንጂ የቁጥር ማስረጃ አልሰጠንም። ምናልባት "ጉዳቸው እንዳይወጣባቸው" ፈርተው ይሆን? ታዲያ ከነዚህ እያንዳንዳቸው በዚህ የስራ መስክ የተሰለፉት 400 የሕወሓት ድርጅቶች ቢያንስ ቢያንስ (10,000,000 ብር) 10 ሚሊዮን የኢትዮ ብር ከገበሬው ላይ ዘርፈዋል ማለት ነው። ወይም ደግሞ 20ዎቹ ድርጅቶች በሞኖፖሊ ቢይዙት ደግሞ እያንዳንዱ የሕወሓት ድርጅት ቢያንስ (200,000,000) 200 ሚሊዮን የኢትዮ ብር ከገበሬው ላይ ዘርፈዋል ማለት ነው። ሕወሓት ገበሬው ላይ ከማዳበሪያ ዕዳ በተጨማሪ በገበሬው ልጆችም ላይ እጅግ ከፍተኛ ምጣኔ ሃብታዊ ቁማር ተጫውቷል። ከምጣኔ ሃብት ዘረፋው በተጨማሪ በገበሬውና በልጆቹ ላይ ያመጣው እያመጣ ያለው የስነ ልቡና ቀውስ ግን ከሁሉም በላይ የከፋ ነው።
>
> በአጭር ጊዜ ውስጥም በርካታ ሚሊየነሮች የተፈጠሩባት አገር በምድራችን ላይ ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ለዚያውም የትግራይ ተወላጆች ብቻ የሆኑ የሕወሓት ደጋፊዎች

ሚሊየነሮች የሆኑባትና "የአፓርታይድ መንደሮች" የተፈጠሩባት ትንግርተኛ አገር ሆናለች። የሕወሓት ደጋፊ በመሆናቸው ብቻ፡ ሳይወጡና ሳይወርዱ፣ በገበያው ዓለም ሳይፈተኑ ሚሊየኖሮችን መፍጠር ይህ ሕወሓት ደጋግሞ እንደሚለው ከሚያካሂደው የ"ሚሊኒየም ልማት" ዋነኛ አካል ነው።

ታዲያ ነገሩ ባይገርምም ከሳውዲ አረቢያ ለተመለሱት 100 ሺ ዜጎቻችን 50 ሚሊየን ብር በበጀት መልክ መያዙን ቴዎድሮስ አድሃኖም ህዳር 13 2006 ተናግሯል። የተዘረፈው 4,000,000,000 ብር (4 ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ለተመላሹ ዜጋ 50,000,000 (50 ሚሊዮን የኢትዮ ብር) ማለትም 1.25% ብቻ። በሌላ አባባል አረብ አገራት የሄዱት 400 ሺህ ወጣቶች ሲሆኑ፣ ባለፉት ጊዜያት ከሳውዲ አረቢያ የተመለሱት 100 ሺህ - ታዲያ ለአንድ አራተኛ ተመላሽ ወጣቶች የተመደበው ገንዘብ 50 ሚሊዮን የኢትዮ ብር ነው። ሕወሓት 50 ሚሊዮን የኢትዮ ብር ከአገሪቱ ካዝና አውጥቷል እንኳን ቢባል "የሂሳብ ቁጥጥር" ስለሌለው ገንዘቡ ወደ ካድሬዎች ኪስ ለመግባቱ ጥርጥር የለውም። የተመለሱትም ወጣቶች በሴተኛ አዳሪነት ወይም በጉልበት ስራ ወይም የደረሱበት አይታወቅም። ሌላ የምጣኔ ሃብት "ሽክም" በአገሪቱ ውስጥ በማስፋፋት የወደፊቱን ትውልድ ማኮላሸት ማለት እንዲህ ነው።

<u>ይህች ናት እንግዲህ የሕወሓት የ"ልማትና ዕዳት" ጨዋታ!!!</u>

ö **ሮቢንሰን ክሩሶ**

ሮቢንሰን ክሩሶ በህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) መሰረት ሊያመርት የሚችለው አማራጭ 2 ኪ.ግ. ፍራፍሬና አትክልት 1.5 ኪ.ግ. የበግ/የፍየል ሥጋ ወይም 2 ኪ.ግ. ፍራፍሬና አትክልት 2 ኪ.ግ. የበግ/የፍየል ሥጋ ይሆናል ማለት ነው።

**ሕወሓት**

ሕወሓትም ካድሬዎችን ማበራከት ወይም ገንዘብ ማሰብሰብ፣ የሚባሉ ሁለት አማራጮች አሉት። ካድሬዎችን ለማበራከት የአንድ-ለ-አምስት ጥፍነጋ እንደ መመሪያ አድርጎ ይዟል። ስራ ለማግኘት፣ መኖሪያ ቤት ለመከራየት፣ ትምህርት ለመከታተል፣ "እስር ቤት" ላለመውረድ፣ ምግብ ለመመገብ፣ የኢትዮጵያን አየር ለመሳብ፣ ፀሐይ ለመሞቅ ወዘተረፈ በአንድ-ለ-አምስት መጠፍነግ እንደ ግዴታ ተደርጎ በ"ሕግ" ረቅቆ እየተሰራበት ነው።

ገንዘብ ለማሰብሰብ ደግሞ በዓባይ ቦንድ ስም ሽያጭና በውጪ አገር የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ነዋሪ አገር ቤት ውስጥ መሬት በነፃ ሰጥቼአችሁ፣ የፈለጋችሁትን ዓይነት ቤት 20 በ80 ወይም 40 በ60 ወይም 90 በ10 የአከፋፈል እቅድ መሰረት ማሰራት ትችላላችሁ እያለ በቅጡ ያልተጠና ግን አጓጊ አርእስቶችን በማንሳት ገንዘብ ለማሰባሰብ ቢሞክርም ካለፉት ዓመታቶች ወዲህ መርዝ እንደ ያዛት ውሻ ከሰባቱ ውስጥ በስድስቱ ክፍለ ዓለማት በተቃውሞ እየተዋከበ ይገኛል። ገንዘብ ማሰባሰቡ አልሆንለት እያለ ነው። <u>ለዓባይ ቦንድ ሽያጭ የተሰበሰበው ወይም የተከማቸው ገንዘብ የመመለሱ ነገር ዜጎች በጥርጣሬ ዓይን ያዩት ገና ከጅምሩ ነው</u>። ሕወሓት መውሰድ እንጂ መስጠት ያላደገበት አመሉ ነውና። ስለሆነም በዚህ ገንዘብ በመሰብሰቡ በኩል ያለው አማራጭ አልሆንልህ ቢለው ሌላ የቀረው በኤፈርት ስም የተዘረፈው ገንዘብ ማውጣት ወይም ወደ ደግሞ ውጭ ይዞ በመሄድ የሕወሓት አባላት በውጭ አገር የተንደላቀቀ የስደት ኑሮ እየከሰከሱ የሚኖርበትን አማራጭ ማስፋት ነው። ሕወሓት ካድሬዎቹን ለማብዛት ደግሞ ገንዘብና አቅም አዲስ ስሌት ይሻል። አዳዲስ አጀንዳዎች ይዞ ብቅ ማለት ይጠበቅበታል። አሊያ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምንጩ እየደረቀ ከሄደ ካድሬዎች የማበራከት አቅሙ ሊያንስ ነው ማለት ነው። ሕወሓት እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ በህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) ህግ መሰረት ስሌቱን ማስላት ይጠበቅበታል።

ክፍል ሦስት

## ፫ ሮቢንሰን ክሩሶ

ሮቢንሰን ክሩሶ መቼም በምግብ ፍለጋ ብቻ አይኖርም። ሮቢንሰን ክሩሶ ከሥጋና ከደም የተፈጠረ የሰው ልጅ ነውና እረፍትና መዝናናትን ይፈልጋል። መፅሐፍ ቅዱስና ካርታዎችን ማንበብ ይፈልጋል። ሮቢንሰን ክሩሶ ብዙ ሰዎች በአውላላ ሜዳ ላይ እንዳሉ አድርጎ በማሰብ ዲስኩር ማድረግ እንደ መዝናኛ አድርጎ ይወስደዋል። ስለዚህ ሮቢንሰን ክሩሶ አሁን ሁለት ትላልቅ አማራጭ አሉት። ሥራ መሥራት ወይም/እና እረፍት። የሮቢንሰን ክሩሶ ሥራ የሚጠቀልለው ፍራፍሬና አትክልት መሰብሰብ፣ እንሰሳት ማደንና እርሻ ማረስን ነው። ሮቢንሰን ክሩሶ የሚዝናናው ደግሞ መፅሐፍ በማንበብ፣ አካባቢውን ለማወቅ በመዞር፣ ወይም ደግሞ ብዙ ሰዎች በአውላላ ሜዳ ላይ እንዳሉ አድርጎ በማሰብ ዲስኩር ማድረግ ነው። እናማ በቀን ከሚኖረው 12 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ጊዜውን በሥራ እና በእረፍት በመከፋፈል መጠቀም ሊኖርበት ነው።

እረፍት የሚወስድበት ጊዜ ረዘም ያለ ከሆነ ምግብ ለመፈለግና ለማዘጋጀት የሚኖረው ጊዜ አጠር ይላል ማለት ነው። ምግብ በመፈለግና በእረፍት መካከል የሚያጠፋው ጊዜ በህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) መሰረት መጣጣም ይጠበቅበታል። ነገር ግን የሮቢንሰን ክሩሶ ምርጫው በህዳጉ ዋጋ መተካካት (Marginal rate of substitution) መሰረት የሚሄድ ከሆነ ደግሞ ሥራ እና እረፍት መተካካት ይችላሉ ማለት ነው። ሙሉ ቀኑን እረፍት መውሰድ ካሰኘው ሆዱ ደግሞ ሊያንጎራጉርበትና ሰውነቱን መዳከሙ ሊከተል ነው። በምግብ እጥረት ሰውነቱ ደከመ ማለት ደግሞ ህመም ጉዝጓዙን ጠቅልሎ ሮቢንሰን ክሩሶ ሊያጠቃው ይችላል። አስታማሚ በሌለበት አገር መታመም የማይታሰብ ነው። ስለዚህ ሰውነቱ በህመም እንዳይጠቃ እና እንዳይደክም ሥራውን በወቅቱ ማከናወን ይኖርበታል።

## ሕወሓት

የሕወሓት አባላቶችም እንደ ሰው ከሥጋና ከደም የተፈጠሩ ናቸውና እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ እነሱም ሁለት አማራጮች አሉአቸው። ሥራ (<u>ገንዘብ መሰብሰብና</u> ካድሬዎችን ማበራከት) እና መዝናናት።

በሮቢንሰን ክሩሶ የምጣኔ ሃብት ውስጥ ገንዘብ ቦታ ወይም ፋይዳ የለውም። "አንተ ገንዘብ ሆይ! እዚያ አገሬ እያለሁ ባገኝህ ኖሮ ብዙ ነገር ልሸምትና ልጠቀምብህ በቻልኩ ነበር። ሃብታም ሆኜ ከአገሬም ለቅቄ ባልወጣሁ ነበር። አሁን ግን ጠልቄ ካለሁበት የብቸኝነት ኑሮ ልታወጣኝ አትችልም።" ብሎ ገንዘብን የረገመው የምጣኔ ሃብቱ በገንዘብ ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን አስረግጦ ሲያስተምረን ነው። በተቃራኒው ደግሞ የሕወሓት-ጦርጦስ የምጣኔ ሃብት እስትንፋስ የተመሰረተው ገንዘብ የመሰብሰቢያ ቀዳዳ በማብዛት ሥራ ላይ ነው።
ስለሆነም ከሕወሓት ሥራዎች አንዱና ዋነኛው ስለሆነው በተለይም ገንዘብ መሰብሰብ በሚለው ነጥብ ዙሪያ አንዳንድ ሁነኛ የገንዘብ ምንጮቹን ለማንሳት ወደድሁ።

ለመሆኑ የሕወሓት የገንዘብ ምንጮች ምንድናቸው?

1) <u>የአገር ውስጥ የገንዘብ ምንጭ።</u> ለመሆኑ የአገር ውስጥ ገቢ በዓመት ምን ያህል ገቢ ይሰበስባል? ይህንን አሃዝ ራሱ ሕወሓት ለዓለም አቀፍ ድርጅት ያሰራጨው ነው[5] ።

ሀ) በ2010 ዓ.ም. ከ43,000,000,000 የኢትዮ ብር (አርባ ሦስት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) በላይ ሰብስቧል።

- ከአገር ውስጥ በቀረጥ ወይም ግብር መልክ የተሰበሰበው 22% ማለትም 9,460,000,000 የኢትዮ ብር (ዘጠኝ ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ሲሆን
- ከውጪ ንግድና ታክስ የተሰበሰበው 33% ማለትም 14,160,000,000 የኢትዮ ብር (አስራ አራት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ከመሬት ግብር / ደሞዝ ወዘተ ታክስ የተሰበሰበ

28% ማለትም 12,040,000,000 የኢትዮ ብር (አስራ ሁለት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) እና

- የተቀረው የተሰበሰበው 17% ማለትም 7,310,000,000 የኢትዮ ብር (ሰባት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) የተሰበሰበው ታክስ ነክ ካልሆነ ገቢ ነው።

**ለ)** በ2012 ዓ.ም. ደግሞ ከ86,000,000,000 የኢትዮ ብር (ሰማንያ ስድስት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) በላይ ሰብስቧል።

- ከአገር ውስጥ በቀረጥ ወይም ግብር መልክ የተሰበሰበው 23% ማለትም 18,920,000,000 የኢትዮ ብር (አስራ ስምንት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ሲሆን
- ከውጪ ንግድና ታክስ የተሰበሰበው 33% ማለትም 28,380,000,000 የኢትዮ ብር (ሃያ ስምንት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ከመሬት ግብር / ደሞዝ ወዘተ ታክስ የተሰበሰበ 28% ማለትም 24,080,000,000 የኢትዮ ብር (ሃያ አራት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) እና
- የተቀረው 14,620,000,000 የኢትዮ ብር (አስራ አራት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) የተሰበሰበው ታክስ ነክ ካልሆነ ገቢ ነው።

Table 1 *(in Million ETH Birr)*

| | 2010 | 2012 |
|---|---|---|
| ከአገር ውስጥ ቀረጥ | 9,460 | 18,920 |
| ከውጪ ንግድና ታክስ | 14,190 | 28,380 |
| ከመሬት ግብር / ደሞዝ | 12,040 | 24,080 |
| ታክስ ነክ ካልሆነ ገቢ | 7,310 | 14,620 |
| **ጠቅላላ ገቢ** | **43,000** | **86,000** |

Source: http://www.tradingeconomics.com

እስቲ እዚህ ላይ አንድ አፍታ ቆም እንበልና ወደ ሂሳብ ስሌት እንግባ። በ2010 ከታክስና ግብር የተሰበሰበው 43 ቢሊዮን የኢትዮ ብር ሲሆን በ2012 ደግሞ 86 ቢሊዮን የኢትዮ ብር ነው። ልብ በሉ 100% ለውጥ አሳይቷል።

እንዴት በሁለት ዓመት ውስጥ ይህን ያህል ልዩነት ያለው ገንዘብ ሊሰበሰብ ይችላል?

እንግዲህ እዚህ ላይ ሌላው የሕወሓት ጨዋታ እንመለከታለን። ሕወሓት የፖለቲካውን የምጣኔ ሃብቱንና የጦር ሰራዊቱን በቁጥጥር ስር አድርጓል። ታዲያ ምን ቀረው? በምጣኔ ሃብት ዝቅተኛ የሆኑ ግን ዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን ላይ ታች የሚሉ "የኢትዮጵያ ዜጎች" ላይ ማተኮር ነበረበት። ለምን? ምክንያቱም "ሌሎቹ የኢትዮጵያ ዜጎች" የያዙትን ቤቶች፣ ሱቆችና መሬታቸውን ይፈልገዋልና። ስለዚህ አነስተኛ የምጣኔ ሃብት ማሻሻያ ንድፍ መንደፍ ነበረበት። የገጠሩና የከተማ መሬት ላይ የ"ሊዝ" ሕግ አዋጅ አወጣ። ካድሬዎቹን የለብለብ የግብር አሰባሰብ "ስልጠና" ሰጠና ከዚያም እነዚህን ካድሬዎቹን ወደ ዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን ላይ ታች ወደሚሉት የኢትዮጵያ ዜጎች ሰደደ። ካድሬዎቹም በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት 10 ሺህ የኢትዮ ብር ንብረት ያለው ሱቅ ከ60 ሺህ የኢትዮ ብር ግብር በላይ ጣሉበት። ሱቁ ውስጥ እኮ ያለው ሸቀጣ ሸቀጥ ተደማምሮ 10 ሺህ ብር የማይሞላ ንብረት ያለው ሱቅ 60 ሺህ ብር ግብር ሲጣልበት የኑሮ እስትንፋሱን ማቆም ማለት ነው። የግብር ግምቱን 60 ሺህ የኢትዮ ብር መክፈል ያልቻለው ቤቱንና ንብረቱን ጥሎ መሰደድ አለበት። አቤት በማለት ስሞታውን የሚያሰማበት ቦታ የለም ወይም አቤት የሚልበት ቦታ ኖሮ በየባለስልጣኖች ቢሮ ቢሄድ ፍትህ እንደማያገኝ ስለሚያውቅ አማራጩ አንድና አንድ ብቻ ነው - ጥሎ መውጣት። ለዘመናት ከሚሰራበት፣ ልጆቹን ካሳደገበት፣ ለቤተሰቡ የዕለት ጉርስ ከሚሸቅልበትና ከሚኖርበት መኖሪያ ቤቱና ሱቁ ጥሎ መሰደድ። አለዚያ ግን መኖሪያ ቤቱና ሱቁ በእሳት ይጋያሉ ወይም በግሬደር ይታረሳል። ባለንብረቶቹ ለበረንዳ አዳሪነት ይዳረጋሉ። ባለንብረቶቹ የካሳ ክፍያ ወይም ምትክ ቦታ

አይሰጣቸውም። ታዲያ በዚህ መንገድ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ነዋሪዎችን ከጨዋታ ውጪ ለማድረግ የተጠቀመበትን የፅዳት ጨዋታ ያስታውሷል። ሌላውን የኢትዮጵያ ዜጋ ካለበት ቤትና ኑሮ እንዲፈናቀል፣ ንብረቱን ደግሞ ለራሱ ደጋፊዎች ቦታ በመስጠት የተጠቀመበት የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ዘዴ ነው።

ሮቢንሰን ክሩሶና ሕወሓት ከሚለያዩባቸው ነገሮች አንዱ የቂመኛነት ባህርይ ነው። ሮቢንሰን ክሩሶ ቂመኛ አልነበረም በተገላቢጦሽ ሕወሓት ግን ቂመኛ ነው። ይህ ዓይነት የቂመኝነት መርዝ የመርጨት ጨዋታ የተካነበትና ከደም ስሩና እስትንፋሱ ጋር የተዋሃደ ነው።
<u>ይህች ናት እንግዲህ የሕወሓት-ጦርጦስ የ"ልማትና ፅዳት" ጨዋታ!!!</u>

2) <u>የውጭ አገር እርዳታና ብድር</u> - የአገሪቱን አንድ ሦስተኛ በጀት በውጭ አገር እርዳታና ብድር ጥገኛ እንደሆነ አሁን አሁን ሕወሓቶችም እየቀለዱ ማረጋገጫ በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የሕወሓት-ጦርጦስ ዓላማ ግን አለ የሚባለውን ንብረት መዝብሮና አጋብሶ ወደ ውጭ በማውጣት ኤፈርት የሚባል አገርየለሽ አገር ለመመስረት ምናልባት ከቻለ አገሪቷን ለመበታተን ካልሆነለት ደግሞ አገሪቱን ሙሉ በሙሉ የውጭ ጥገኛ አድርጎ ዝንተ ዓለም ለማሰር ነው። አገራችን ኢትዮጵያ የውጭ ብድር በዓለም ባንክ መረጃ መሰረት <u>እስከ 2012 በትንሹ የ10 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር (200 ቢሊዮን የኢትዮ ብር) ባለ ዕዳ ነች።</u>[6]

ይህ ማለት ደግሞ መጪው ኢትዮጵያዊው ትውልድ መኖሪያ አገር አይኖረውም። ታሪክ አይኖረውም። ኢትዮጵያዊው "እሱነቱን" ረስቶ አሜሪካን ውስጥ እንደሚገኙት "የህንድ ዝርያዎች" በተወሰነ ቦታ ብቻ እንዲኖሩ ሲፈረድባቸው ወይም አውሮፓ ውስጥ ሁለተኛና ሦስተኛ ዜጋ ሆነው እንደሚኖሩት "ጂብሲዎች" ማለትም "አገር ገንቢ" ሳይሆኑ በድህነት፣ በሌብነት፣ በሴተኛ አዳሪነት፣ ወኔ የለሽ የ"አገር ተጧሪዎች" የሚፈጠሩበት መንገድ ለማመቻቸት ጠንክሮ እየሰራ ነው። አሁን አሁን ላይ ስናየው የሕወሓት-ጦርጦስ ዓላማ በመጠኑም ቢሆን እየተሳካለት ነው።

3) <u>በውጭ አገር ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ</u> - በውጭ አገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን በግምት 2 ሚሊዮን ይደርሳሉ። ታዲያ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት ለዘመዶቻቸው የሚልኩትና ለአንዳንድ አገራቸው ነክ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚያወጡት ወጪ በዓመት ከ4 እስከ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይደርሳል። በማንኛውም መንገድ ቢሆን ይህ ገቢ የሚወድቀው በሕወሓት እጅ ነው። ገንዘቡን በጥሬ ብር ቢልኩ ወይም ለጉዞ ቢጠቀሙበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚው ሕወሓት ነው።

4) <u>የውጭ ንግድ</u> - ለመሆኑ የምግብ እህሎች፣ ፍራፍሬዎች፣ የከብት እንስሳቶች ከኢትዮጵያውያኑ እየነጠቀና በረሃብ ዜጋውን እየገረፈ ወደ ውጭ የሚጋዘው የምጣኔ ሃብት ጥቅሙ ምን ያህል ቢሆን ነው? ይህንን ጥያቄ በእጅጉ ለማጤንና ለመፈተሽ እንዲረዳ የውጭ ንግድን በጭላንጭሉ ለማሳየት ልሞክር።

ኢትዮጵያ ወደ ውጪ ከምትልካቸው (Export) ውስጥ - የግብርና ጥሬ ምርቶች፣ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች፣ የፋብሪካ ምርት መሳሪያዎች፣ እና የመድንና ፋይናንስ አገልግሎቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ወደ አገር ውስጥ ከምታስገባቸው (Import) ነገሮች ውስጥ - የግብርና ጥሬ ምርቶች፣ የምግብ እህል ጥራጥሬ ሸቀጦች፣ የነዳጅ ምርቶች፣ የፋብሪካ ምርትና መሳሪያዎች፣ እና የመድንና ፋይናንስ አገልግሎቶች ናቸው።

ሮቢንሰን ክሩሶ የቃኘውን ነገር ሁሉ የራሱ ንብረት በማድረግ "ንጉሥ"፡ ብሎ ራሱን እንደሚሾም ሁሉ ሕወሓትም 95-96% የአገሪቱን ድርጅቶች ጠቅልሎ መያዙን እንዳለ ታሳቢ በማድረግ ሁለት ጥያቄዎችን ልወርውር። መቼም አገር ውስጥ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ዋጋቸው የማይቀመስ መሆኑ እሙን ነው። ስለሆነም፣

1) ለመሆኑ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ወደ ውጭ በመላክ ለአገሪቱ ምን ጥቅም አመጣ? የምግብ እህሎች፣ ፍራፍሬዎችና የሲጋ ምርቶች ለምን ተወደዱ?
2) ባጠቃላይ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ወደ አገር ውስጥ ከሚገባውና ከሚላከው (Import - Export) ሸቀጥ አንፃር አስተዋፅዖው ምን ያህል ነው?

እንደ ምሳሌ አሁንም ሕወሓት ያሰራጨውን አሃዝ እንመልከት[7]።

ከ2004 እስከ 2011 የተገኙትን ቁጥሮችና (Import and Export figures) በተጨማሪም ለስሌት እንዲያመች በ2004 1 የአሜሪካን ዶላር = 8.60 የኢ.ትዮ ብር በ2011 ደግሞ 1 የአሜሪካን ዶላር = 17.2 የኢ.ትዮ ብር ከ2004-2011 በአማካይ 1 የአሜሪካን ዶላር = 11.6 የኢ.ትዮ ብር ምንዛሪ ተጠቅሜያለሁ።[8]

ይህ አሃዝ Table 2 ላይ እንደሚታየው ባለፉት 7 ዓመታት ማለትም እ.አ.አ ከ2004 - 2011 ያሉትን የውጭ ሽያጭ (Export) እና ወደ አገሪቱ ከውጭ የገባው (Import) ያጠቃልላል።

ለጠቅላላ ግንዛቤ እንዲረዳን ባለፉት ሰባት ዓመታት ከ2004 እስከ 2011 እ.አ.አ. ወደ ውጭ አገራቶች የተላኩትንና ከውጭ አገር የገቡትን በአማካይ ስንመለከት ወደ አገር ቤት የገባው ሸቀጥ በ5,238,942,571.43 የአሜሪካን ዶላር ይበልጣል። በሌላ አነጋገር ወደ ውጭ የሚላከው ሸቀጥ ከውጪ ከሚገባ ሸቀጥ ጋር ሲወዳደር በእጅጉ ተመጣጣኝ አይደለም። ከውጪ ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ሸቀጣ ሸቀጦች ውስጥ የፋብሪካ ምርትና መሳሪያዎች 68% የነዳጅ ምርት 18% የምግብ ሸቀጥ ደግሞ 11% ይዘዋል። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው የሕወሓት ድርጅቶች በአካፋ እየዛቁ ወደ አገር ቤት ሲያስገቡና ሲያስወጡ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ግን በሻይ ማንኪያ እየመጠኑ እንዲያስገቡና እንዲያስገቡ የምጣኔ ሃብት መመሪያ መነደፉ እሙን ነው።

## Average Export and Import from 2004 thr 2011 Calculated

Table 2

| Descriptions | Export Average | Import Average |
|---|---|---|
| Agricultural raw materials (% of merchandise exports - imports) in Ethiopia | 215,282,288.57 | 62,399,454.83 |
| Food (% of merchandise exports - imports) in Ethiopia | 1,298,062,300.79 | 795,691,209.94 |
| Fuel (% of merchandise exports – imports) in Ethiopia | 41,128.29 | 1,250,687,831.80 |
| Insurance and financial services (% of commercial service exports - imports) in Ethiopia | 20,676,835.50 | 31,396,776.57 |
| Manufactures (% of merchandise exports - imports) in Ethiopia | 153,920,481.57 | 4,720,233,279.51 |
| Ores and metals (% of merchandise exports - imports) in Ethiopia | 19,728,393.86 | 86,245,447.34 |
| Total | 1,707,711,428.57 | 6,946,654,000.00 |

Source: http://www.tradingeconomics.com

እንግዲህ የምግብ ሸቀጦች፣ እህሎችና ፍራፍሬዎችን ነጥዬ በጥልቀት ላሳይ፣

፩) ወደ ውጭ አገር ከሚላኩት የምግብ ሸቀጦች ውስጥ የሚጠቀልለው ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ጫት፣ ወርቅ፣ የአበባ ምርቶች፣ የምግብ ጥራጥሬዎችና ሌሎችንም ያካትታል።

Table 3

| Export | 2004 | 2011 | Change |
|---|---|---|---|
| Food exports (% of merchandise exports) in Ethiopia | 935,312,400 | 2,253,425,000 | 141% |

Source: http://www.tradingeconomics.com

እዚህ Table 3 ላይ እንደተመለከተው

- በ2004 ዓ.ም. ወደ ውጭ የተላከው ሸቀጦችና የምግብ ሸቀጥ እህሎችና ፍራፍሬዎች (Exported food items) 935,312,400.00 የአሜሪካን ዶላር ወይም 8,044,000,000.00 የኢ.ት ብር (ስምንት ቢሊዮን የኢ.ት ብር) ነው።
- በ2011 ዓ.ም. ደግሞ 2,253,425,000.00 የአሜሪካን ዶላር ወይም 38,749,000,000.00 የኢ.ት ብር (ሠላሳ ስምንት ቢሊዮን የኢ.ት ብር) ነው።
- ከ2004 — 2011 ባሉት ዓመታት ውስጥ በአማካይ በዓመት ወደ ውጭ የተላከው 1,298,062,300.79 የአሜሪካን ዶላር ነው።
- የ2004 አሃዝ ከ2011 አሃዝ ጋር ሲወዳደር ወደ ውጭ የተላኩት ሸቀጦችና የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች (Exported food items) በ141 % ለውጥ አሳይቷል።

እዚህ ላይ ልብ በሉ ይህ አሃዝ ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት በሊዝ አግኝተው የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎችን በጓሮ በር ወደ አገራቸው የሚልኩትን (Export food items) እንደ ሳውዲ አረቢያንና ሕንድን የመሳሰሉት አገራት ወደ አገራቸው የሚልኩት የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎችን አይጨምርም። አንድ የአረብ ጋዜጣ [9] በወጣው ዘገባ መሰረት በ2013 ዓ.ም. ብቻ ሳውዲ አረቢያ በየወሩ 10 ሺ ቶን ፍራፍሬዎችን ወደ አገሯ በነፃ ልካለች። በዓመት በትንሹ 1.2 ሚሊዮን ኩንታል ወደ ሳውዲ አረቢያ ብቻ በነፃ ይላካል። ይህ በገንዘብ ሲተመን 240,000,000 የአሜሪካን ዶላር 4,560,000,000 የኢ.ት ብር (ከአራት ቢሊዮን የኢ.ት ብር በላይ) ነው።

፪) አሁን ደግሞ ባለፉት ሰባት ዓመታት ማለትም ከ2004 እስከ 2011 ባሉት ጊዜያቶች ወደ አገሪቱ ውስጥ ከውጭ አገራት የገባው (Import food items) የምግብ ሸቀጦችን እንመልከት።

Table 4

| Import | 2004 | 2011 | Change |
|---|---|---|---|
| Food imports (% of merchandise imports) in Ethiopia | 434,431,200.00 | 1,315,718,400.00 | 203% |

Source: http://www.tradingeconomics.com

Table 4 ላይ እንደሚታየው

- በ2004 ዓ.ም. ከውጭ ወደ አገሪቱ የገባው (Imported food items) የምግብ ሸቀጦችና ጥራጥሬዎች 434,431,200.00 የአሜሪካን ዶላር ወይም 3,736,000,000.00 የኢ.ት ብር (ሦስት ቢሊዮን የኢ.ትዮ ብር በላይ) ነው።
- በ2011 ዓ.ም. ደግሞ ከውጭ ወደ አገሪቱ የገባው (Imported food items) 1,315,718,400.00 የአሜሪካን ዶላር ወይም 22,630,000,000.00 የኢ.ት ብር (ሃያ ሁለት ቢሊዮን የ ኢ.ትዮ ብር በላይ) ነው።

- በነዚህ ዓመታት ውስጥ ወደ አገሪቱ ውስጥ ከውጭ አገራት የገባው (Import food items) የምግብ ሸቀጦች በዓመት በአማካይ 795,691,209.94 የአሜሪካን ዶላር ነው።
- የ2004 አሃዝ ከ2011 አሃዝ ጋር ሲወዳደር በ2011 ከውጭ የተሸመተው (Imported food items) የምግብ እህሎች በ203% ለውጥ አሳይቷል።

ታዲያ እነዚህን የመሳሰሉትን የቁጥር ለውጦችን ለተመለከተ ለምሳሌ 141% ወይም 203% የለውጥ ቁጥሮችን ለተመለከተ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ወደ ሌላ ዓለም አውጥቶ መሸቀሉና የምግብ እህሎችና ጥራጥሬዎች ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚያዋጣ ሊመስለው ይችላል።

በነገራችን ላይ የ141 ወይም 203% "ለውጥ አሳይቷል" ሲባል የምጣኔ ሃብት እድገት /Development/ አለ ማለት አይደለም። በምጣኔ ሃብት እድገት /Development/ ልዩ ትርጉም አለውና።

፫) እዚህ ላይ የምግብ ሸቀጦች ሆነው ግን መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ ክፍሎች ብዬ ነጥዬ የማወጣቸው የምግብ ጥሬጥሬ እህሎች ለምሳሌ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ወዘተ ፍራፍሬዎች፣ የከብት እንስሳት የሥጋ ምርቶችን ያካትታል። ሌላው የግብርና ምርቶችና ሸቀጦች የሆኑት ደግሞ ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ጫት፣ ወርቅና የአበባ ምርቶች ለጊዜው መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ ክፍሎች ውስጥ አላካተትኩም። ምክንያቱም ከላይ በጥያቄ እንዳነሳሁት መሰረታዊ የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ለምን ተወደዱ? የሚለውን ጥያቄ አጥርቶ ለመመለስ ይረዳልና።

ከታች Table 5 [10] ላይ እንደምንመለከተው ከ2007 እስከ 2011 ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በአማካይ በዓመት ወደ ውጭ የተላከው መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ብቻ ሲተመኑ 126,670,000.00 የአሜሪካን ዶላር ነው።

Table 5 *(in Million USD)*

| Food Exports Description | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | Average |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Meat & Meat Products | 15.50 | 20.90 | 26.60 | 34.00 | 63.30 | 32.06 |
| Fruits & Vegetables | 16.20 | 12.80 | 12.10 | 31.47 | 31.50 | 20.81 |
| Live Animals | 36.80 | 40.90 | 52.70 | 90.70 | 147.90 | 73.80 |
| | | | | | | |
| Total | 68.50 | 74.60 | 91.40 | 156.17 | 242.70 | 126.67 |

Source: National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011 (in Million USD)

ባለፉት አምስት ዓመታት ማለትም ከ2007 እስከ 2011 ባሉት ጊዜያቶች ወደ አገሪቱ ውስጥ ከውጭ አገራት የገቡት (Import food items) አጠቃላይ መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን ስንመልከት ደግሞ በአማካይ በዓመት ከውጭ አገራት የተሸመተው የምግብ ጥራጥሬ እህሎች ሲተመን 452,700,000.00 የአሜሪካን ዶላር ነው።[11]

Table 6 *(in Million USD)*

| Food Imports | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **Description** | *2007* | *2008* | *2009* | *2010* | *2011* | **Average** |
| Cereals የጥራጥሬ ሸቀጦች [12] | *344.42* | *557.48* | 513.1 | 196 | 652.5 | 452.7 |
| | | | | | | |
| Import Total | **344.42** | **557.48** | **513.1** | **196** | **652.5** | |

1 Source: National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011 (in Million USD)
2 Calculated based on FAO MT information for 2007 and 2008

ከውጪ አገራት ወደ አገር ቤት የሚገቡት የጥራጥሬ ምግብ ሸቀጦች (Cereals) ስንዴ፣ በቆሎ፣ ሩዝና ባቄላን ያጠቃልላል።

በተለይ የውጪ ንግድን በተመለከተ ወደ ውጪ የሚላኩትንና ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ሸቀጦች በየዘርፉ በመለያየትና ነጥሎ በማስላት ጥቅምና ጉዳቱን ማመዛዘን ወይም ወጭና ትርፉን ማስላት (Cost-benefit analysis) እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ወደ ውጪ ይላካሉ እንዲሁም መሰረታዊ የምግብ ጥራጥሬ እህሎች ወደ አገር ውስጥ ይገባሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርት ላይ እንዲህ ያለ የመመዘኛ ትንተና በየዘርፉ ባለማየቴ በእጅጉ አሳዝኖኛል። እስቲ ለማመዛዘን እንዲረዳን Table 7 ን እንመልከት።

- ከ2007 እስከ 2011 ባሉት 5 ዓመታት ውስጥ ወደ ውጪ የተላከው መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ 126 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ነው።
- ከ2007 እስከ 2011 ባሉት 5 ዓመታት ውስጥ ወደ አገር ውስጥ የገቡት መሰረታዊ የምግብ ጥራጥሬ ሸቀጦች 452.7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ነው።
- የውጭ ንግድ ጠቃሚ ውጤት አምጥቷል የሚባለው ወደ ውጭ የተላከው ሸቀጥ (Exports) ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ሸቀጥ (Imports) ወጪ ሸፍኖ ሲገኝ ነው። በዚህም መሰረት ከ2007 እስከ 2011 የመሰረታዊ ምግብ ጥራጥሬ ሸቀጦች ውጤት እንደሚከተለው ነው።

Table 7 *(in Million USD)*

| Description | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | Average |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Food Export Total | 68.50 | 74.60 | 91.40 | 156.17 | 242.70 | 126.67 |
| Food Import Total | 344.42 | 557.48 | 513.10 | 196.00 | 652.50 | 452.70 |
| Balance of Payments | (275.92) | (482.88) | (421.70) | (39.83) | (409.80) | (326.03) |

- እንግዲህ Table 7 ላይ እንደምናየው ወደ ውጭ የተላከው የምግብ ሸቀጥ አንሶ ከውጭ የገባው ከመጠን በላይ በዝቶ - በ2007 - 275.92 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ፤ በ2008 - 482.88 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ፤ በ2009 - 421.70 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ፤ በ2010 - 39.83 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ፤ እና በ2011 - 409.80 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ አምጥቷል።

- ከ2007 እስከ 2011 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ መሰረት ባለፉት 5 ዓመታት በአማካይ በዓመት 326.03 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ከአራት ቢሊዮን የኢትዮ ብር) በላይ ኪሳራ በአገሪቱ ላይ አምጥቷል። በዚህ ስሌት መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ውጪ መላክ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።

ሕወሓት መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ወደውጪ በመላክ በወገኖቻችን ላይ ከፍተኛ በደል እያደረሰ መሆኑን መናገር የማይችሉት ቁጥሮችም እየመሰከሩበት ይገኛል። ይህ የውጭ ንግድ በተለይም መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ንግድ መመሪያ ከፖለቲካ ጥቅም የመነጨ እንጂ ከምጣኔ ሃብት ጥቅም አንፃር የተሰላ አይደለም። በወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለው በደል ምጣኔ ሃብታዊ በደል ብቻ ሳይሆን የሰብኃዊነት በደል እያደረሰ ይገኛል። የምግብ ሸቀጥ ወደ ሳውዲ አረብያና ህንድ በነፃ "በባለቤትና በልማት ስም" ይጋዛል በአንፃሩ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በምግብ እጦት ምክንያት ምግብ "በጉርሻ" ይሸምታል። የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ አለንጋ እንዲገረፍ ሕወሓት-ጦርጦስ ፈርዶባታል።

"በልማት ስም ፅዳት" ማለት ይህ ነው!!!

፬) ምናልባት መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ ወደ ውጭ አገር መላክ የውጪ ምንዛሪ ለማግኘትና አገሪቷ ያለባትን ዕዳ ለመቀነስ ይረዳል ለሚሉት አንድ ነጥብ ልጨምር። Table 8 እና 9 ኙን ይመልከቱ።

ሀ) ከ2007 እስከ 2011 ዓ.ም. በአማካይ ባለፉት አምስት ዓመታት አጠቃላይ የምግብ እህሎችንና ፍራፍሬዎችን ወደ ውጭ የተላኩትንና (Exported food items) ወደ አገሪቷ ውስጥ የገቡትን (Imported food items) የምግብ ጥአጥሬዎች ስንመለከት ደግሞ በአማካይ ልዩነቱ 379,000,000 የአሜሪካን ዶላር ነው። ማለትም ወደ ውጭ አገራት የተላከው የምግብ ሸቀጥ ብዛት አለው። ስለዚህ ወደ ውጭ የተላከው የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ከውጭ አገራት የሚገቡትን ጥራጥሬዎች ዋጋ ስለሸፈነ ትርፍ አምጥቷል ማለት ነው።

ለ) እስቲ አሁን ደግሞ ጠቅላላ ወደ ውጪ የተላከውንና ወደ አገር ውስጥ የገባውን ሸቀጥ (Export - Import Commodities) ማለትም የግብርና ጥሬ ምርቶች፣ የምግብ እህሎችና ጥራጥሬዎች፣ የፋብሪካ ምርት መሳሪያዎች፣ እና የመድንና ፋይናንስ አገልግሎቶች እንመለከት።

- ከ2007 እስከ 2011 ዓ.ም. ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ አገሪቱ ከውጭ አገራት የገባው (Imported Commodities) በአማካይ በዓመት 5,616,000,000 የአሜሪካን ዶላር ነው።
- ከ2007 እስከ 2011 ዓ.ም. ባሉት አምስት ዓመታት ወደ ውጭ የተላከው ሸቀጥ (Exported Commodities) በአማካይ በዓመት 1,387,000,000 የአሜሪካን ዶላር ነው።

## Export and Import Analysis

Calculated from 2007 - 2011

Table 8 *(in Million USD)*

| ***Descriptions*** | ***Average Export*** | ***Average Import*** | ***Balance of Payments*** | ***Dist'n in %-age*** |
|---|---|---|---|---|
| Agricultural raw materials (% of merchandise imports) in Ethiopia | 163.32 | 46.50 | 116.82 | -2.76% |
| Food (% of merchandise imports) in Ethiopia | 1,049.34 | 670.20 | 379.14 | -8.97% |
| Fuel (% of merchandise imports) in Ethiopia | 0.04 | 1,013.81 | (1,013.77) | 23.97% |
| Insurance and financial services (% of commercial service imports) in Ethiopia | 19.75 | 23.96 | (4.22) | 0.10% |
| Manufactures (% of merchandise imports) in Ethiopia | 138.08 | 3,788.57 | (3,650.49) | 86.33% |
| Ores and metals (% of merchandise imports) in Ethiopia | 17.04 | 73.18 | (56.14) | 1.33% |
| | | | | |
| Total | 1,387.57 | 5,616.23 | (4,228.66) | 100.00% |

Source: http://www.tradingeconomics.com (in Million USD)

ሐ) ከ2007 እስከ 2011 ባሉት አምስት ዓመታት የምግብ ጥራጥሬ እህሎችና ወደ አገር ውስጥ የሚገባው (Imported food items) እና ወደ ውጭ የተላከውን ሸቀጥ (Exported food items) ለጠቅላላው ወደ ውጭ ለሚላከውና ለሚገባው ሸቀጥ (Export - Import Commodities) ያደረገው አስተዋፅዖ ሲገመት 8.97% ብቻ ነው።

ይህንን የ8.97% ውጤትና አስተዋፅዖ ሰፋና ዘርዘር አድርጌ ለማሳየት ልሞክር። Table 9ን ይመልከቱ።

## Food Export and Import Analysis

Calculated from 2007 - 2011 Table 9 (in Million USD)

| Descriptions | Average Export | Average Import | *Balance of Payments* | Dist'n in %-age |
|---|---|---|---|---|
| ሌሎች የምግብ ክፍሎች - Other Food items | 922.74 | 217.50 | 705.24 | -16.68% |
| መሰረታዊ የምግብ ክፍሎች -Basic Food items | 126.60 | 452.70 | (326.10) | 7.71% |
| **Food merchandise in Ethiopia** | **1,049.34** | **670.20** | **379.14** | **-8.97%** |

ሀ) ከ2007 እስከ 2011 ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ውጭ የተላኩትና ወደ አገር ቤት የገቡትን የምግብ ሸቀጦች መሰረታዊ የምግብ ክፍሎችና ሌሎች የምግብ ክፍሎች በሚል ተከፍለዋል።

- መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ ክፍሎች (Basic Food items) ብዬ የምላቸው የምግብ ጥሬጥሬ እህሎች ለምሳሌ ጤፍ፤ ስንዴ፤ በቆሎ ወዘተ ፍራፍሬዎች፤ የከብት እንሰሳት የሥጋ ምርቶችን ነው።
- ሌሎች የምግብ ክፍሎች (Other Food items) ደግሞ የግብርና ምርቶችና ሸቀጦች የሆኑት ቡና፤ የቅባት እህሎች፤ ጫት፤ ወርቅና የአበባ ምርቶችን ያካትታል።

ለ) Table 9 ላይ ያሉት ቁጥሮች የሚገልፁት፤

1) ሌሎች የምግብ ክፍሎች (Other Food items) ብቻ ለውጭ ንግድ ቢውሉ ኖሮ ለውጭ ንግድ ያላቸው ተዋፅዖ በዓመት በአማካይ 16.68% ይሆን ነበር። በሌላ አባባል 705.24 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ዕዳ መክፈል ይችል ነበር። ምክንያቱም ወደ ውጭ የተላኩት የምግብ ሸቀጦች በ705.24 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብልጫ ስላላቸውና ወደ አገር ውስጥ የገቡትን የምግብ ሸቀጦች ወጪ ሸፍኗልና።

2) መሰረታዊ የምግብ ክፍሎች ለውጭ ንግድ ያላቸው ተዋፅዖ 7.71% ነው። ማለትም 7.71% (በዓመት በአማካይ 326.10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) ተጨማሪ የውጭ ዕዳ በአገሪቱ ላይ አምጥቷል። ወደ አገር ውስጥ የገባው መሰረታዊ የምግብ ሸቀጥ በ326.10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብልጫ አሳይቷል። መሰረታዊ የምግብ ክፍሎች (Basic Food items) ለውጭ ንግድ በመዋሉ ብቻ በዓመት በአማካይ የ4.2 ቢሊየን የኢት ብር ባለ ዕዳ አድርጎናል።

የአፋር ግመሎችና እንሰሶቻችን እንኳን "የኢትዮጵያን ባንዲራ ቀለም ያውቃሉ" ብለው አንድ አባት እንደመሰከሩ ሁሉ - የውጭ ንግድ መሰረታዊ የምግብ ክፍል ቁጥሮችም "ወደ ውጭ ተልከን ኪሳራ ከምናመጣ እዚሁ ቀርተን ኢትዮጵያውያን አምራቾቻችን ይመገቡን" እያሉ በግልፅ ቋንቋ ይናገራሉ።

እንግዲህ እንደ **ቁጥሮቹ** እኔም ድምፄን ከፍ አድርጌ ጡሩንባዬን እየነፋሁ የሚከተለውን አውጃለሁ።

አዋጅ! አዋጅ! አዋጅ!
ሰሚ ጆሮ ያለው የሕወሓት አባልም ሆነ ደጋፊ ይስማ።
መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ውጭ አገራት መላክ ለአገሪቱ ዕዳ እንጂ ጥቅም አላመጣም።
ወደ ውጭ አገር የሚላከው መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ለአገር ውስጥ ፍጆታ ይዋሉ።
የኢትዮጵያን ህዝብ በምግብ አትበድሉት።

እነዚህ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የወጡት አሃዞች እንደሚያሳዩት የምግብ እህሎችና ፍራፍሬዎች ወደ ውጭ መላኩ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። እንዲያውም አገሪቱ በምግብ በኩል ያለባትን ችግር አባባሰ። መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ለውጭ ንግድ በመቅረባቸው ለአገሪቱ የሚያስገኘው አንዳችም ጥቅም የለውም። የአገሪቱን ህዝብ በረሃብ ለመግረፍ የወጣ የሕወሓት-ጦርጦስ የምጣኔ ሃብት ንድፍ ነው።

ከታሪክ እንደምንረዳው ህዝባቸውን ምግብና ውሃ በመንፈግ የጥቃት ንድፍ የሚነድፉት በሽፍትነት ያሉ ወይም ጦር መሳሪያ ያነገቱ ወንጀለኞች ብቻ ናቸው። በዓለም አገሮች ታሪክ ውስጥ መንበረ ስልጣን ከጨብጠ በኋላ ለሚያስተዳድረው ህዝብና አገር ደንታ የሌለው ቢኖር ባንዳውን ሕወሓት የመጀመሪያው ያደርገዋል። የሕወሓት-ጦርጦስ ፍልስፍና በአገር ክህደት በኩልም የዓለምን ክብረ ወሰን ሰበሯል። የሕወሓት-ጦርጦስ ፍልስፍናም ከ21ኛው ምዕተ ዓመት የዓለም የምጣኔ ሃብት ንድፍ ጋር የማይጣጣምና ጊዜው ያለፈበት ነው።

<u>ይህች ናት እንግዲህ የሕወሓት-ጦርጦስ የ"ልማትና ዕዳት" ጨዋታ!!!</u>

ለማጠቃለል ያህል እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ የሕወሓት አባላቶችም እንደ ሰው ከሥጋና ከደም የተፈጠሩ ናቸውና ሁለት አማራጮች አሉአቸው። ሥራ (<u>ገንዘብ መሰብሰብ /</u> ካድሬዎችን ማበራከት) እና መዝናናት።

ሕወሓቶች እንዴት ገንዘብ እንደሚያሰባስቡ በመጠኑም ቢሆን አየን። ካድሬዎችን የሚያበራክቱት ደግሞ በአንድ ለአምስት ጥፍነጋ ወይም መሬትና ገንዘብ በመስጠት ወይም በአባይ ቦንድና በማዳበሪያ ወይም በሌላ ቁሳቁስ ዘዴ የዕዳ ተያዥ በማድረግ ነው።

ክፍል አራት

## 3.3 የህዳጉ ዋጋ ለውጥ (ካለፈው የቀጠለ)

*መዝናናት ማለት በሕወሓት-ጦርጦስ ፅንሰ ሃሳብ የተለየ ትርጉም አለው። መዝናናት የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በሕወሓት መዝገበ ቃላት ትርጉሙ የሰውን ስብዕናን መድፈር፣ በብሔርና በቋንቋ መከፋፈልና እርስ በርስ ማጣላት፣ ሙስናን በአገሪቱ ውስጥ ማስፋፋት፣ መሬት ለውጭ ዜጎች በሊዝ ማቀራመት - ኢትዮጵያውያዊ ነዋሪውን በማባረር ማለት ነው፣ የአገሪቱን የረጅም ጊዜ ህልውና መድፈር፣ የኢትዮጵያውያንን ስነ ልቡና መስበር፣ የኢትዮጵያዊውን ንብረት ወደ ትግራይ እንደተጋዘ ሁሉ አሁን ደግሞ ወደ ኤፈርት ንብረትነት ለውጦ ወደ ውጭ አገር ማጋዝ፣ የወደፊቷን ትግራይ ለመመስረት መሠረቱን መጣል፣ ጠንካራ ትምህርት ለምርጥ የትግራይ የሕወሓት ወዳጆች ብቻ ማዳረስ፣ የምጣኔ ሃብት እድገት ቁጥር እየፈበረኩ ማብዛት፣ በትናንሽና ትላልቅ ብሔረ ሰቦች ላይ የስነ ልቡናዊ ጫና በማሳደር የ"ነፃ አውጪ" ግንባሮች እንዲመሰረቱ መጣርና ወደፊት ሰላም በአገሪቱ ውስጥ እንዳይፈጠር የጦርነት መድረኮች እንዲስፋፉ መሰረት መጣል ወዘተ ነው። እነዚህ ዓይነተኛ የሆኑ የሕወሓት የመዝናኛ መርሃ ግብሮቹ ናቸው። የሕወሓት የመዝናኛ ጊዜውና የደስታ ጮቤ የሚረግጠው ሌላው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ስቃዩ ሲበዛ ሲያይ ነው። የባንዳዎች ብቀላ ማለት ይህ ነው።*

*የምጣኔ ሃብት እድገት ቁጥር እየፈበረኩ ማብዛት የሚለው መርሃ ግብር ከምጣኔ ሃብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በጥቂቱ መጥቀስ አስፈላጊ ይመስለኛል። በተለይም በአገራችን ውስጥ በዓይናችን ስለምናያቸውን የተገነቡትን ህንፃዎችና መንገዶች በማንሳት አነስተኛ ምጣኔ ሃብታዊ ትንተና ላቅርብ።*

> *የከረመ ባይሆንም ባለፉት አጭር ዓመታት ከ*12 *ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር*[13] *ወይም* 220 *ቢሊዮን የኢትዮ ብር በላይ በሕወሓት ባለስልጣናት ተዘርፎ መውጣቱን ፀሐይ የሞቀው ዜና ነው።*
>
> *እስቲ ለመሆኑ በተዘረፈው* 220 *ቢሊዮን የኢትዮ ብር ምን መስራት ይቻል ነበር?*
>
> *አሁን እየተካሄደ ካለው "ልማት-ፅዳት" ጋር ላነፃፅር በዚያውም እግረ መንገዳችን ስለ ተመዘበረው ገንዘብ አጠቃቀም ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይረዳኛል። አሁን በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ ግንባታ እየተከናወነ ነው በማለት ሕወሓት ደረቱን ነፍቶ የሚናገረው ነገር አለ። አንድ "መንግሥት" ነኝ የሚል አካል "ይህንን ሰርቼያለሁ" ብሎ ደረቱን አይነፋም። "ምን?...ያለበት ዝላይ አይችልም" እንደተባለው ካልሆነ በስተቀር። በርግጥም ህንፃዎች ተገንብተዋል - የንብረቶቹ ባለቤትና የገንዘብ ምንጭነቱ ግልፅ ቢሆንም ማለትም ባለንብረቶቹ ጥቂት የሕወሓት ትግራይ ተወላጆች የገንዘብ ምንጩ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ አንጡራ መሆኑ ቢታወቅም። ከህንፃው ጋር አብረው የሚሄዱ የውሃና የመብራት ችግሮች ዓይናቸው እንዳፈጠጡ ቢያሳብቁም። አሁንም በርግጥ የመኪና መንገዶችም ተሰርተዋል - በጊዜያዊነት ለሶስትና ለአራት ዓመታት የማይዘልቁ ቢሆንም ማለትም የጥራት ችግር ቢኖርም። ታዲያ ሕወሓት ከዚህ ግንባታ ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ብዙ የገንዘብ ትርፍ አጋብሶ ወደ ውጭ ዓለም አግዞአል። የህንፃ ግንባታ ቢካሄድም ሕወሓት ትልቅ ትርፍ አጋብሶበታል። እንዴት?*
>
> *በቅርቡ ይፋ በተደረገው ጥናት መሰረት የኤፈርትና የአላሙዲን ድርጅቶች የኢትዮጵያን* 94-96% *ምጣኔ ሃብት ይዘውት ይገኛሉ። ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን* 4-6% *ምጣኔ ሃብት አለው ማለት ነው። ታዲያ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ አቅራቢ ድርጅቶች የተያዙት በኤፈርትና*

በአላሙዲን ናቸው። ቤት አሰሪውም፤ ቤት ገንቢውም፤ መንገድ ሰሪውም፤ ቁሳቁስ አቅራቢውም፤ ንብረት ተቆጣጣሪውም፤ ህግ አውጪውም፤ ህግ አስፈፃሚውም ሁሉንም ሕወሓት ነው። እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ ማለት ነው። ሮቢንሰን ክሩሶ አራሽም፤ አምራችም፤ አዳኝም፤ ሸማችም፤ ለባሽም፤ ተጠቃሚም፤ ተመጋቢም፤ ጦረኛም፤ ተዋጊም ነው። በአጭሩ ሮቢንሰን ክሩሶ ሁሉንም ነው።

የምጣኔ ሃብት እቅድ እንደ ሀ ሁ ብዬ አጭር ትንተናና ስሌት ላቅርብ - ከዓለም ታሪክ እንደምንማረው ከጥፋት ልማት ይፀነሳል፤ ከውድቀት እድገት ይመጣል። እና ለትምህርት እንዲሆን ከጥፋትና ከውድቀት ልነሳ። የሕወሓት ቁጥር ሁለት ጥፋቱ ዝርፊያው ነው። (ቁጥር አንድ ጥፋቱ ለሰው ልጅ ያለው የዘቀጠ ፍልስፍናውና የሚፈፅማቸው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶቹ ናቸው። የዚህ መጣጥፍ ትኩረት ምጣኔ ሃብት ስለሆነ ቁጥር ሁለት ጥፋቱ ላይ ዝርፊያውን በጥልቀት እንመለከታለን።)

እንዲያው ለመሆኑ ሕወሓት በዘረፈው 220 ቢሊዮን የኢትዮ ብር እንዴት ያሉ ግንባታዎች ሊካሄዱ ይችል ነበር?

በተለያዩ መንገዶች ለማሳየት እንዲረዳኝ የሚከተሉትን ነጥቦች ላስቀምጥ።

በምጣኔ ሀብት ተመራማሪዎች ዘንድ “Assumption” የተከበረ ፅንሰ አሳብ ነው። “Assumption” ማለት “ነገሮችን እንዳሉ አድርጎ መቀበል” ማለት ነው። ወይም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር በመበታተን ቀለል ባለ መንገድ ለማሳየት የሚጠቀሙበት መንገድ ነው። ታዳጊ አገሮች አሁን የደረሱበት ከፍተኛ የምጣኔ ሃብት ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት የ“Assumption” ፅንሰ ሃሳብ መንገዶችን ስለተከተሉና አሁንም በመከተል ላይ ስለሆኑ ነው። አንድ የልማት ዝርዝር በ 220 ቢሊዮን ብር ከመጀመራችን አስቀድሞ የሚከተሉት ጥቂት “ነገሮችን እንዳሉ አድርገን እንቀበል”።

1) የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት ችግር ያለመኖርና አብዛኛዎቹ አቅርቦቶች አገር ውስጥ ቢመረቱ፤
2) ግንባታው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ያሳተፈ ቢሆን፤
3) በጥሬ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ንረት ያለመኖር፤
4) አገርን ማልማት ከሁሉም የኅብረተሰቡ የኑሮ እድገት ጋር አብሮ የማጣመር ዝግጅትና ጥናት ቢኖር፤
5) የሚኖረው አስተዳደር እንደ ሕወሓት እንደ ነጋዴና ሙሰኛ ሳይሆን እንደ አስተዳደሪ ብቻ ሆኖ ስራውን አከናወነ ቢባል፤
6) የቤቶች ግንባታ ትመና የቀን ሰራተኛ፤ የውሃ፤ የኮሬንቲና የመፀዳጃ ወጪዎችንም ያጠቃልላል ቢባል፤
7) የሕወሓት / ኤፈርት ድርጅቶች ገቢያውን በአጠቃላይ በሞኖፖልና በብቸኝነት አልያዙትም ቢባል፤
8) ቅንና አሳቢ መንግሥታዊ አስተዳደር ቢኖር፤
9) ለግንባታው ወጪ ሙሉ በሙሉ የሚውለው በሕወሓት የተዘረፈው 12 ቢሊየን ዶላር ነው ብንል፤
10) አቅም ኖሯቸው ቤት ማሰራት የሚችሉ ዜጎችን እዚህ እቅድ ውስጥ አይገቡም ብለን ብናሰላ፤

እነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ በመመርኮዝ አራት ተናጠል የሆኑ ግንባታዎችን በምሳሌነት ላንሳ፤ የመኖሪ ቤቶች ግንባታ፡ የፎቆች ግንባታ፡ የመንገዶችና የግድቦች ግንባታ፤ እና በተጨማሪ የትላልቅና አነስተኛ እንዱስትሪዎች ግንባታ በሚል።

## ሀ) የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ

በተጨማሪም ለዚህ ስሌት እንዲረዳን አንድ ተጨማሪ መረጃ ልጨምር፤

በ2013 በቀረበው አንድ ጥናት ላይ እንደተመለከተው በአገራችን ውስጥ ከ17 ሺህ ህዝብ በላይ የሚኖርባቸው 145 ከተማዎች አሉ። እዚህ ላይ ትላልቅ ከተሞችንና አዲስ አበባ ይጨምራል። እነዚህ ትላልቅ ከተማዎች ውስጥ ያለው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 10.2 ሚሊዮን ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ከ 4-5 ሚሊዮን ህዝብ ይኖራል። በአንድ ቤት ውስጥ በአማካይ 4 ወይም 5 ሰዎች ይኖራሉ እንበል። በዚህ ስሌት አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ቤቶች አሉ።

በአጠቃላይ በ145 ከተማዎች ውስጥ ቢያንስ ከ 2 ሚሊዮን ቤቶች በላይ ይኖራሉ። እያንዳንዱን ቤት በአማካይ ለመገንባት 50 ሺህ (ሲሶው ለዕቃ፤ የቀረው ለሠራተኛ) ይጨርሳል ብለን እናስላ። በዚህ ስሌት በ145 ከተማዎች ውስጥ 2 ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት 100 ቢሊዮን የኢት ብር ያስፈልጋል እንበል። (መረጃ 1 - የቤቶች ግንባታ ወጪ እቅድ ይመልከቱ)

በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ደግሞ ከ65 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ይኖራል ብንልና በትንሹ 12 ሚሊዮን ቤቶች ያስፈልጋሉ ብንል የእያንዳንዱ ቤት ግንባታ 10 ሺህ የኢትዮ ብር ይፈጃል ቢባል። 120 ቢሊዮን የኢትዮ ብር ያስፈልጋል። (መረጃ 1 - የቤቶች ግንባታ ወጪ እቅድ ይመልከቱ) ስለዚህ በ220 ቢሊዮን ብር 14 ሚሊዮን ቤቶችን መገንባት ይቻላል።

መረጃ 1 - የቤቶች ግንባታ ወጪ እቅድ

| *እቅድ* | *የቤቶች ብዛት - በሚሊየን* | *ለእያንዳንዱ ቤት ወጪ* | *የኢት ብር - ጠቅላላ ወጪ - በሚሊየን* |
|---|---|---|---|
| የከተማ ቤቶች | 2 | 50,000 | 100,000 |
| የገጠር ቤቶች | 12 | 10,000 | 120,000 |
| ጠቅላላ | 14 | | 220,000 |

*መረጃ* 2 - ለእያንዳንዱ ቤት የሚወጣው ወጪ ዝርዝር

መረጃ 2 - የቤቶች ግንባታ ወጪ እቅድ ዝርዝር

| ዝርዝር | ለከተማ ቤት | ለገጠር ቤት |
|---|---|---|
| ለሰራተኛ ክፍያ በሰዓት | 15 | 10 |
| በቀን የስራ ሰዓት | 8 | 8 |
| ለሰራተኛ ክፍያ በቀን | 120 | 80 |
| ለአንድ ቤት ግንባታ የሚፈጀው ቀን / ሰዓት | 5 ቀን / 40 ሰዓት | 3 ቀን / 24 ሰዓት |
| አንድ ቤት ለመገንባት የሚፈልገው የሰው ብዛት | 40 | 25 |
| ለአንድ ሰው በአንድ ቤት ግንባታ ክፍያ | 600 | 240 |
| | | |
| ጠቅላላ ለሰራተኛ የሚከፈል ወጪ | 24,000 | 6,000 |
| ለቁሳቁስ የሚወጣ ወጪ | 17,000 | 3,300 |
| መጠባበቂያ ወጪ | 9,000 | 700 |
| | | |
| ለእያንዳንዱ ቤት ግንባት የሚወጣው ወጪ | **50,000** | **10,000** |

*መረጃ* 3 - በአጠቃላይ ለሰራተኛና ለቁሳቁስ የሚወጣው ወጪ ሲደመር 220 ቢሊዮን ነው።

መረጃ 3 - የቤቶች ግንባታ ወጪ እቅድ ዝርዝር

| ዝርዝር | ለከተማ ቤት | ለገጠር ቤት | | ዝርዝር | ጠቅላላ በሚሊዮን |
|---|---|---|---|---|---|
| አንድ ቤት ለመገንባት የሚፈጀው ሰዓት | 40 | 24 | | ለ2 ሚሊዮን ቤቶች ለመገንባት የሚፈጀው ሰዓት | 368 |
| አንድ ቤት ለመገንባት የሚፈልገው የሰው ብዛት | 40 | 25 | | ለ2 ሚሊዮን ቤቶች ለመገንባት የሚፈልገው የሰው ኃይል ብዛት | 380 |
| ለአንድ ሰው በአንድ ቤት ግንባታ ክፍያ | 600 | 240 | | | |
| | | | | | |
| ጠቅላላ ለሰራተኛ የሚወጣ ወጪ | 24,000 | 6,000 | | ለ380 ሚሊዮን ጠቅላላ ሰራተኛ የሚወጣ ወጪ | 120,000 |
| ለቁሳቁስ | 17,000 | 3,300 | | ለቁሳቁስ | 73,600 |
| መጠባበቂያ ወጪ | 9,000 | 700 | | መጠባበቂያ ወጪ | 26,400 |
| | | | | | |
| **ጠቅላላ** | **50,000** | **10,000** | | **ጠቅላላ** | **220,000** |

እዚህ ላይ ጠቅለል አድርጌ ነጥቦቹን ላቅርብ፤

1) አስራ አራት ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት 368 ሚሊዮን ሰዓታት ይፈጃል። ማለትም በቀናት ሲሰላ 46 ሚሊዮን ቀናት ይፈጃል ማለት ነው። ነገር ግን በጠቅላላው የ20 ዓመታት እቅድ ተብሎ ቢያዝና በየዓመቱ 6 ቢሊዮን ብር ቢመደብ ለ19 ሚሊዮን የሰው ኃይል የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

2) አስራ አራት ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት 380 ሚሊዮን የጉልበት ኃይል ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 5 ጊዜ እጥፍ የጉልበት ኃይል ያስፈልጋል ማለት ነው።

3) አስራ አራት ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት 120 ቢሊዮን ብር ለጉልበት ኃይል ይወጣል። ከላይ በቁጥር 1 ላይ እንደተጠቀሰው የ20 ዓመታት እቅድ ተብሎ ቢያዝና በየዓመቱ 6 ቢሊዮን ብር ቢመደብ 19 ሚሊዮን የሰው ኃይል ያስፈልጋል። ይህም ማለት ደግሞ ለዚህ ሁሉ ሠራተኛ ምግብ፤ መጠጥ፤ ልብስና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች አቅራቢ ያስፈልጋል። ስለሆነም ይህንን ተከትሎ ደግሞ ሌሎች የሥራ መስኮች እንዲከፈቱና ገንዘብ በአገሪቱ ውስጥ እንዲዘዋወር ይረዳል። የሥራ መስኮች መከፈት ደግሞ ለብዙ ኢትዮጵያውያኖች የሥራ መስክ ስለሚከፍት ከዚህ ለጥቆም የትምህርት የጤናና የግብር መስኮች እንዲጎለብቱና እንዲጠናከሩ ያግዛል። መጠነ ሰፊ የምጣኔ ሃብት እድገትም እንዲኖር ያደርጋል።

4) ከላይ መጠባበቂያ ገንዘብ የተባለው 20.4 ቢሊዮን ብር ምናልባት ሥራው እየተካሄደ ባለበት ወቅት ያልታሰቡ ነገሮች ቢያጋጥሙ ተብሎ ለችግር ጊዜ የተቀመጠ ገንዘብ ነው። ለምሳሌ የተፈላጊ ምርት ዋጋ ማሻቀብ፤ የተፈጥሮ ችግሮች ቢያጋጥሙ ወዘተ

5) በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለ75 ሚሊዮን ነዋሪ በግምት 14 ሚሊዮን መኖሪያ ቤቶች ያስፈልጋሉ ቢባል ሕወሓት በዘረፈው 220 ቢሊዮን የኢትዮ ብር ሁሉንም ቤቶች መገንባት ይቻል ነበር። ሕወሓት በዘረፈው በ220 ቢሊዮን ብር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አዲስ ቤት ሊኖረው በቻለ ነበር። ልማት ማለት ይህ ነው! የሕወሓት ሌቦች በመዘበሩት ገንዘብ ብቻ አሁን ተጋኖ ከሚሰበክልን ልማት እጅግ ብዙ ጊዜ የበለጠ ልማት በአገራችን ላይ ይታይ እንደነበር ከላይ ካየነው አነስተኛ ምሳሌ ለመረዳት ይቻላል።

ልማት ለአገር! ልማት በሁሉም ለሁሉም ማለት እንደዚህ ሲሆን ነው!

**ለ) የፎቆች ግንባታ፤**

በዚህ በሕወሓት በተዘረፈው 220 ቢሊዮን ብር የፎቆች ግንባታ ብቻ ይካሄድ ቢባል። አንድ 300 ቤቶች (እያንዳንዱ ቤት 3 ወይም 4 ክፍል) ያለው ባለ 10 ፎቅ 50 ሚሊዮን ብር ይፈጃል ብለን እናስላ። በዚህ በተዘረፈው 220 ቢሊዮን ብር 4,400 ፎቆችን በመላ አገሪቱ ውስጥ መገንባታ ይቻላል።

**ሐ) የመንገዶችና የግድቦች ግንባታ፤**

በዚህ በተዘረፈው 220 ቢሊዮን ብር የመንገድና የግድብ ግንባታ ብቻ ይካሄድ ቢባል። ለእያንዳንዱ ኪሜ የአስፋልት ንጣፍ 100,000 ብር ይፈጃል ቢባል ለ50,000 ኪ.ሜ. 5 ቢሊዮን ብር ይፈጃል። አንድ የግድብ ግንባታ ደግሞ በግርድፉ 50 ቢሊዮን ብር ይፈጃል ብንል በትንሹ አራት ግድቦች በ200 ቢሊዮን ብር መስራት ይቻላል። በሕወሓት ባለስልጣናት ተዘርፎ በወጣው ገንዘብ 50,000 ኪ.ሜ. የአስፓልት መንገድና በትንሹ አራት የወንዝ ግድቦችን መስራት ይቻላል። አገርን ማልማት ማለት እንዲህ ነው።

**መ) የትላልቅና አነስተኛ እንዱስትሪዎች ግንባታ**

በዚህ በተዘረፈው 220 ቢሊዮን ብር የትላልቅና አነስተኛ እንዱስትሪዎች ግንባታ ብቻ ይካሄድ ቢባል፤ 30 ትላልቅ እንዱስትሪዎች 1 ቢሊዮን ካፒታል ያላቸው፤ 100 የሚሆኑ መካከለኛ እንዱስትሪዎች 100 ሚሊዮን ካፒታል ያላቸው፤ 16,000 የሚሆኑ መለስተኛ መካከለኛ እንዱስትሪዎች 5 ሚሊዮን ካፒታል ያላቸው፤ 100,000 አነስተኛ እንዱስትሪዎች 1 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያላቸው ግንባታዎችን ማካሄድ ይቻላል።
ከዚህ በተጨማሪም በዚህ የእንዱስትሪ መስክ በትንሹ 7 ሚሊዮን ለሚሆን የሰው ኃይል የስራ መስክ መፍጠር በተቻለ ነበር። አገርን ማልማት ማለት እንዲህ ነው።

ተጨማሪ የዘረፋ መስኮች

በነካካ እጅ ሌሎች ከምጣኔ ሃብት ዘረፋ ከተንሰራፋባቸው መስኮች ውስጥ በጥቂቱ ልጥቀስ፤ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን በተንቀሳቃሽ ስልክ ብቻ ላይ ያለው ዘረፋ በሁለት መልክ ማየት ይቻላል።

1) ኅብረተሰቡን የሚለዋወጠውን መረጃ ለመያዝ ወይም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር፤
2) በገንዘብ በኩል ደግሞ "የሚታለም ላም" መሆኑን የተረጋገጠ ነው። እንዴት? የሚለውን በምሳሌ ላስረዳ

   ከተንቀሳቃሽ ስልክ የሚገኝ ገቢ፤ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በሳምንት በአማካይ በትንሹ 25 - 50 የኢት ብር ለቴሌፎን ካርድ ያወጣል ብንልና በኢትዮጵያ ውስጥ 15 ሚሊዮን ሕዝብ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ አለ ብለን እናስብ። ከቴሌፎን ካርድ ሽያጭ ብቻ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን በዓመት ከ23 - 40 ቢሊዮን የኢት ብር ወይም 1.3 —2.0 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያገኛል። ሕወሓት "የሚታለም ላም" አለኝ የሚለው ይህ ነው።

   ነገር ግን የዚህ ገንዘብ 1% ማለት 300 ሚሊዮን ለምርምርና ለጥናት ቢውል ኢትዮጵያ ውስጥ የሞባይል ምርቶችን ማምረት በተቻለ ነበር። አገር ውስጥ በዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ የተማረ ኃይል በማደራጀት አገሪቷ አሁን ካለችበት ከፍተኛ አዘቅት እንድትወጣ ይረዳ ነበር። አገራችን የቻይና የምርት ትርፍራፊ ጠባቂ ከመሆን ትተርፍ ነበር። የሕወሓትና በአጠቃላይ የአፍሪካ መሪዎች ጭንቅላት የሚያውጠነጥነው "የበትረ መንግስት ስልጣኔን እንዴት ላስጠብቅ?" በሚል ፍልስፍና ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ዘላቂ መፍትሄ ላይ እምብዛም ሲጨነቁ አይታይም።

"የስኳር ፋብሪካ ግንባታ ልማት"ም ቢሆን አገርና ታሪክ አጥፊና መሰሪ የሕወሓት የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ነው። የስኳር ልማት ሰፋፊ መሬቶችን ይሻሉ። ስለዚህ ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎችን አነስተኛ ብርቅዬ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማጥፋት ያለመ በሕወሓት-ጦርጦስ የተነደፈ አገር አጥፊ ፖሊሲ ነው።

በቅርቡ ይፋ በወጣው መረጃ መሰረት ሕወሓትና ድርጅቶቹ 100,000 ህፃናቶች ልጆች ከአገራችን በማስወጣት የተጧጧፈ ንግድ ያካሂዳል። መቼም የሚሰቀጥጥ ዜና ነው። ከነዚህ ውስጥ 2,000 ልጆች በየዓመቱ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ ለእያንዳንዱ ልጅ 46,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም 874,000 የኢት ብር ሲጠይቅ ቢያንስ 92,000,000 የአሜሪካን ዶላር ወይም ቢያንስ ሁለት ቢሊየን የኢት ብር ይሰበስብበታል።

በአንፃሩ ግን ከላይ ባስቀመጥኳቸው የ"Assumption" ነጥቦች ቢሚሉ እነዚህን 100,000 ህፃናት በቀን ሃያ የኢት ብር መድቦ እስከ 20 ዓመት ተንከባክቦና በትምህርት ለማበልፀግ ወጪው በጠቅላላው 500 ሚሊዮን የኢትዮ ብር ብቻ ነው። ሕወሓት በአንድ ዓመት በዘረፈው 1.7 ቢሊየን የኢት ብር ቢያንስ 350,000 ህፃናትን በመንከባከብ ሃያ ዓመት እድሜ እስከሚደርሱ ማቆየት ይቻላል። የአገር ልማትና "ትውልድ የማዳን ፖሊሲ" ማለት ይህ ነው። ህፃናትን መሸጥ ግን የወሮበሎችና የማፍያዎች ድርጊት ነው።

ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ለውጪ በማቅረብ የሚያገኘው እርዳታም የዋዛ አይደለም። ቤቶችና የንግድ መደብሮች ላይ እሳት በመልቀቅ የሚያተርፈው ትርፍ እንዲሁ ቀላል አይደለም።

በሥራና በመዝናናት መካከል ያለው መጣጣም በህዳጉ ዋጋ ለውጥ (Marginal rate of transformation) መሰረት ማድረግ ይጠበቅበታል። ነገር ግን ሕወሓት እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ ምርጫው በህዳጉ ዋጋ ተተኪ (Marginal rate of substitution) ህግ መሰረት ከሆነ ደግሞ ሥራ እና መዝናናትን በመተካካት ሊይዘው ይችላል ማለት ነው። ስለሆነም ሕወሓትም ሁለት አማራጮች አሉት። ሥራና መዝናናት። ሥራ መስራት ሳይችል ሲቀር መዝናናት ያበዛል። በመሠረቱ የሕወሓት ሥራም ሆነ መዝናናት ሁለቱም መስመሮቹ አገር ጎጂና ህዝብ አጥፊ ናቸው።

፯ **ሮቢንሰን ክሩሶ**

ከላይ እንደገለፅኩት የሮቢንሰን ክሩሶ ታሪክ የተመሰረተው በአሌክሳንደር ስልከርክ የአራት ዓመት አራት ወራት ቆይታ ላይ ነው። እና አሌክሳንደር ስልከርክ ከአራት ዓመታት አራት ወራት ቆይታ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ ከሰው ጋር ተቀላቅሏል። በዚህ ባለንበት ዘመን በህይወት ባይኖርም በምናባችን "እንኳን ከሰው ጋር ለመገናኘትና ለመቀላቀል አበቃህ" እንበለው። አሁንም ደጋግመን "እንኳን ከዘመዶች ለመቀላቀል አበቃህ" እንበለው። ሮቢንሰን ክሩሶ ከሰዎች ጋር ይኖር ነበር፤ ከሰዎች ጋር መኖር ይፈልግም ነበር። ሮቢንሰን ክሩሶ ከሰዎች ርቆ ለረጅም ጊዜ በብቸኝነት የኖረ ግለሰብ ስለነበር ከሰዎች ጋር ተቀላቅሎ ለመኖር አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል። በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ ከሰው ልጅ ጋር ተቀላቅሎ የመኖር ተፈጥሮአዊ ግዴታ አለበት። ለብዙ ጊዜያቶች ያህል ከሰው ተለይቶ በብቸኝነት መኖሩ ትልቅ የፀባይ ልዩነት ይፈጥራል። አሌክሳንደር ስልከርክ ብቸኝነት አስወግዶ ከህብረተሰቡ ተቀላቅሎ ለመኖር መጠነኛ የስነ ልቡና ችግር ያጋጥመዋል።

**ሕወሓት**

ሕወሓት-ጦርጦስ የሕይወት ዘመኑ ሲያበቃ ስልጣኑን ለቆ መሄዱ የማይቀር ነው። በጥቂት ጊዜያቶች ውስጥ ከህዝቡ መቀላቀሉና የብቻ ኑሮውን በስልጣን ላይ ሳይሆን እንደ ህዝቡ እሱም በተራው ታች መውረጃው ተቃርቧል። በዚህ ወቅት ላይ ሆነን በምናባችን "እንኳን ወረድክ" እንበለው።

ሕወሓት ብቸኝነት አስወግዶ እንደ ሮቢንሰን ክሩሶ ከህብረተሰቡ ተቀላቅሎ ለመኖር የስነ ልቡና ችግር አለበት። በሌላ አባባል ሕወሓት በተፈጥሮው ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ ለመኖር የስነ ልቡና ችግር አለበት። ብቸኝነት ይወዳል። የኢትዮጵያ ጥላቻ ስላለበትና ከገንዘብ

ጋር በፍቅር ስለከነፈ ብቸኝነቱን የበለጠ እንዲገፋበት አድርጎታል። በርግጥም ተቀላቅሎ ለመኖር የስነ ልቡና ችግር አለበት።
መቼም የዋሆች ነንና አሁን ላይ ሆነን ይህንን ሃሳብ ላንቀበል እንችላለን። እንዲያውም ተባብረን እንመልሰው የምንልም አንጠፋም። ይህ ጤነኛ አስተሳሰብ ነው። ሆኖም ግን አሁንም አስረግጨ የምለው ሕወሓት በተፈጥሮው የስነ ልቡና ችግር አለበት። በብቸኝነት ሲገዛ፣ ሲዘርፍ፣ ሲፈልጥ፣ ሲቆርጥ ኖሯል። የብቸኝነቱ ጫና ሚዛኑ አድልቷል። ወደ አብሮ የመኖር ጎዳና ለመመለስ ቢፈልግ እንኳን የብቸኝነት ተፈጥሮው አይፈቅድለትም። ስለሆነም አብሮ የመኖር ችግር ያለበት ገና ከአፈጣጠሩ ነው። ለሕወሓት "በሰላም አብሮ መኖር" ማለት ተፈጥሮው አከሰመ ማለት ነው።

ታዲያ ስለ ምጣኔ ሃብት ስናወሳ አንድ ነገር ልብ እንበል። ሕወሓት በድርጅቱ በኤፈርት በኩል የሰበሰበው ገንዘብና የአገር ሃብት ወደ ውጪ አግዞ የሌላ አገር ማበልፀጊያ አድርጓልም፣ እያደረገም ይገኛል። (ለዚህም በምድረ አሜሪካ በተለያዩ ስቴቶች በካድሬዎቹ በኩል እየገዛና እየከፈታቸው ያሉት ድርጅቶች ዓይነተኛ መረጃዎች ናቸው።) የኢትዮጵያ ካዝና ባዶ አድርጎ ይሄዳል። የኢትዮጵያ ልጆች ባለ ዕዳ አድርጓቸዋል። ለእርስ በርስ ጦርነትም በሩን ከፍቶ ይሄዳል። ለጊዜውም ቢሆን ኢትዮጵያ ችግር ውስጥ ማለትም በፖለቲካ፣ በምጣኔ ሃብት እና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ መግባቷ የማይቀር ነው። ይህንን ቀውስ ለመታደግ ከወዲሁ መላ ምቶችን ማስቀመጥና ይህ ቢመጣ እንደዚህ ያሉ መንገዶች ይኖራሉ በማለት መንገድ መጠቆሙ የምጣኔ ሃብትና የሌሎች መስክ ምሁራን ግዴታ ነው።

ይህንን በተመለከተ ሁሉም ምሁራኖች በተለይም የምጣኔ ሃብት ምሁራን ችግሩንና መፍትሄውን በተመለከተ በነፃ አስተያየታቸውን መሰንዘርና የጠለቀ ጥናት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አንድ ላይ ተባብሮ አንድ የምጣኔ ሃብት የጥናት ማዕከል በውጭ አገር በማቋቋም ከሌሎች አገራቶች ተሞክሮ ለማስተማርም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። (አገር ቤት ያለው ወይም የነበረው የምጣኔ የጥናት ማዕከል በቅርብ ጊዜ በሕወሓት ምን ዓይነት አደጋ ላይ እንዳለ የታወቀ ነው።) ራስንና ህብረተሰቡን ለሚቀጥለው የአገር ግንባታ ማዘጋጀት በእጅጉ ያስፈልጋል። ራስን ማወቅ፣ ታሪክን ማወቅ፣ ተምሮ ማስተማር፣ የውጭ አገራትን ተሞክሮ መገንዘብ፣ ኢትዮጵያዊነትን ጠብቆ ማቆየት የዚህ ትውልድ ግዴታ ነው።

***ማጠቃለያ***

በአንዲት ደሴት ላይ አንድ ሰው ራሱ አምራች ራሱ ገዢና ተጠቃሚ የሆነበትን የምጣኔ ሃብት እናያለን። ሮቢንሰን ክሩሶ ራሱ የፈለገውን ምርት ለማምረት ይወስናል ያመረተውንም ምርት ተጠቃሚ የመሆን ጉጉት፣ ፍላጎት ግዴታ አለበት። ይህ የአንድ ሰው የምጣኔ ሃብት ተምሳሌነት ነው። ይህ የሮቢንሰን ክሩሶ የአንድ ሰው የምጣኔ ሃብትና ሕወሓት የሚመሳሰሉት በምጣኔ ሃብት፣ በአስተዳደርና፣ በስነ ልቡና ደረጃ ነው። በምጣኔ ሃብት በኩል በዓይኑ ለሚቃኘው ቦታ ሁሉ ባለቤት ነው። ለሚያየው ነገር ሁሉ ንጉስ ነው። ነገር ግን አይኑን ላፍታ የከደነ ወይም ላንዳፍታ ያሸለበ ዕለት የሚደርስበትን ችግር በቁሙ ስለሚያስበረግገው በስነ ልቡና ችግር የተወጠረ ነው። "መዝናናቱ" ደስታ የሚሰጠውን ያህል ሲበረግግም ቦታ አይበቃውም። ሕወሓት ሲበረግግ ግን አገሪቱን እርቃኗን ስለሚያስቀራት በሚወዷት ልጆቿ እንደምትታደግ ተስፋው በጭላንጭሉ ይታየኛል።
ስለሆነም ለጊዜው ሕወሓትን ለመገንደስ ከሚደረገው የፖለቲካ ትግል እኩል የሚከተሉትንም ምጣኔ ሃብታዊ ትግል በስራ ማዋል ተገቢ ይመስለኛል።

1) ጉቦኞች ለፍርድ የሚቀርቡበትን መድረክ ለማዘጋጀት ጠቃሚ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣

2) ማናኛውንም ዓይነት በግንባታ ስም የሚካሄዱትን ዘረፋዎችንም ሆነ "ልማታዊ" ግንባታዎችን ማስቆም፤ የአባይ፣ የቤቶች፣ የባቡር፣ የመንገድ ወዘተ ግንባታ ዘርፍ ላይ አለመተባበር እንዲሁም "መዋጮ" ማስተጓጎል፤
3) በውጪ አገር ሕወሓት አባላቶች ስለሚገዙት ንብረቶች ጠቃሚ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤ ይህ መረጃ ማሰባሰብ የሚጠቅመው ምናልባት ለወደፊቱ በሕወሓት የተዘረፉት ንብረቶች ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው ለአገሪቱ ጥቅም የሚውሉበትን መንገድ ለመቀየስ ይረዳል።
4) በአገር ቤት ውስጥ በአንድ ለአምስት የታቀፉ ኢትዮጵያውያን አባላቶች አስፈላጊ ምጣኔ ሃብታዊ መረጃዎችን ማሹለክ የሚችሉበትን ተጨማሪ መድረኮችን ማመቻቸት፤ በአሁኑ ሰዓት በኢሳት ሬዲዮ በኩል ከኅብረተሰቡ የሚመጡትን መረጃዎች እንዳሉ ሆነው ማለት ነው።
5) ምሁራኖች በምጣኔ ሃብትና በአስተዳደር ዘርፍ በኩል ሰፊ የሆነ ትምህርታዊ መድረኮችን ማዘጋጀት፤ ኅብረተሰቡንም ማስተማር፤ በተለያዩ አገሮች የሚገኙትን የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ ማኅበራት መሪዎችም ስለ ስነ-አስተዳደር (በተለይም ችግሮችን ስለመቅረፍ) ተምረው ሌሎች የማኅበራት አባላቶችም የሚማሩበትን መንገድ መቀየስ፤
6) ተተኪ ትውልድ ለመተካት በውጭ አገር የተወለዱትን ህፃናትንና ወጣቶችን ስለኢትዮጵያ ታሪክ ማስተማር፤ ኢትዮጵያዊነትን እንዲያዳብሩ የትምህርት መድረኮችን ማዘጋጀት።
7) አሁን ያለውን የተማረ ኃይል በተለያየ የምጣኔ ሃብት ዘርፍ አሰማርቶ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ማዘጋጀት እንዲሁም አሁን ያለውን የዘረኞች የትምህርት እቅድ የሚገለብጥና ሁሉን ዜጋ የሚያሳትፍ የትምህርት እቅድ መምከርና ማዘጋጀት።

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው። አሜን።

* የዚህ መጣጥፍ አቅራቢ በትላልቅ የግል ኩባንያዎች ውስጥ በፋይናንስ ዘርፍ ልምድ ያካበተና በምጣኔ ሃብት ዶክትሬትም አለው።

አስተያየት ካሎት በ tayele@yahoo.com ሊያገኙኝ ይችላሉ። @ Aug 2014

## ዋቢ ሰነዶች

[1] አማርኛ መዝገበ ቃላት -የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል - አአዩ - የካቲት 1993- ገፅ 363
[2] Robinson Crusoe by Daniel Defoe, published 1719
[3] Source: http://wikipedia.org/wiki/Robinson_Cruso_economy
[4] Source: http://www.ethiomedia.com/2012_report/yezer_manzer.pdf
[5] Source: http://www.erca.gov.et
[6] Source: http://en.wikipedia.org/wiki/List_of_countries_by_external_debt
[7] http://www.tradingeconomics.com
[8] National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011
[9] Source http://mereja.com/forum/
[10] National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011
[11] National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011
[12] Source: 1) National Bank of Ethiopia Annual Report 2009-2010, 2010-2011 and 2) http://www.foodsecurityportal.org/ethiopia
[13] Source: http://www.gfintegrity.org